# ምዕራፍ ሦስት

አቶ ገብረብሩክ በቀጠሮቸው መሠረት ከጓደኞቸው ጋር አወንደላጤ ጓደኞቸው ቤት ተገናኝተው ልዩና ሚስጥራዊ ዝግ ስብሰባ እካሂደው በሃሳብ እየተፋጩ ነዉ:: አንዱ "መክብብን ድራሹን ማጥፋት አለብን፡ ሌላው ለምን ጣጣችንን እናበራክታለን፡ ሁለተኛ ቤቴም ሆነ እዚህ ሰፈር እንዳላይህ፡ ይህ ሁሉ ጣጣ የመጣው ባንተ የተነሳ ነው ብለህ ለምን አታባርረውም፡ ሌላኛው የተፈነከትከውን ታክም ብሎ ሃኪም ቤት አስገብቶ እዚያ እስከዘላለሙ እንዲያሽልብ ጥሩ መርፌ ማስጠት ነው ::

"አንተ ደግሞ 'ከአፍ ከወጣ አፋፍ' የተባለውን አታስታውስም:: ሚስጥራችንን ማጥበብ ነው እንጂ ማስፋት በምንም አይነት ሁኔታ አይበጅንም:: እያንዳንዳችን ስንት አሰደናቂ ሚስጥራዊ ሥራ እንደሰራን እናውቀዋለን:: የሠራነውንም ስህተታችንን ላለመድገም መጣር አለብን:: የኢሚግሬሽን ሴትዮ ችግር ውስጥ የከተትካት በአንተ ዝርክርክነት እንደሆነ መዘንጋት የለብህም" እያለ ሲቀጥል፡ ሌላው "አቋረጠውና

"ታዲያ ምን ይሁን ነው የምትለው መፍትሄ አምጣ" ሲለው፤

አ.. መፍትሄማ አለኝ:: ይህን ውዳቂ ለማጥፋት የተኛበት ሆስፒታል ከታወቀ ከምግብ ጋር ጥሩ ቅመም ስጥቶ



በቀላሉ ማስተናገድ ነው::" እየተባባሉ በሃሳብ ይፋጫሉ፡ ከብዙ መነዛነዝ በሁዋላ፤

"ትርሲትን የወሰዷትን ለዎችና የመታውን ሰው ያስታወሰ እንደሆነ አንዳችን ወይም ከኛ ውጭ ታማኝ ሰው ፈልገን ራሱን እንደ ነጭ ለባሽ አስመስሎ ማውጣጣት መቻል አለብን:: ጠያቂው በጣም ሊረሳው የማይገባው ነገር ቢኖር ፍጹም ለመክብብና ለትርሲት የቆሙ፡ የነሱ ለቅሶ የሚያስለቅሰው፡ ጭንቀታቸው የሚያስጨንቀው የሚሆን ጥሩ ቲያትረኛ መሆን አለበት:: በዚህ ዘዴ ተጠቅመን የደበደበኝንና ትርሲትን የወሰዷትን አስታውሳለሁ ብሎ ትንሽ ፍንጭ ከሰጠ ነገ ዛሬ ሳንል ድራሹን ለማጥፋት የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ለመጠቀም መዘጋጀት አለብን::"

ወ/ሮ አረጋሽ መክብብ ያለበትን ሆስፒታል ለባለቤቷ ተናግራ ከኢምፔሪያል ሆቴል አካባቢ ባልቻ ሆስፒታል የሚወስድ ሂሊኮፍተር ቢኖር ኖሮ ያለ ንብረቷን ሽጣ ቶሎ ብትደርስ ምኞቷ ነበር:: እጇን ታውለበልባለች፡ ታክሲው ሁሉ እየሞላ አያለፋት፡ ለጥቂት ጊዜ ከተንገላታች በሁዋላ፡ አንድ አንስተኛ ታክሲ ኮንትራት ይዛ ባልቻ ሆስፒታል እንደደረሰች ከበር ጀምራ መክብብ የተኛበት ክፍል እስከምትደርስ ሁሉንም እየጠየቀች ስትደርስ፡ እበሩ ጋ ቆማ የነበረችውን ነርስ "ይቅርታ የእኔ እህት፡ 'መክብብ' የሚባል ታካሚ ለመጠየቅ ነበር የመጣሁት" አለቻት፡ እንባዋን መንታ መንታውን እያወረደች:: ነርሷም "ወይ የእኔ እመቤት አይዞሽ እንደዚህ አትሁኝ ለከፋ የሚሰጥ ነገር የለውምኮ" አለቻት:: ወ/ሮ አረጋሽ

አይዞሽ ስትባል የባሰ ሆዷ ባባና እንባዋ ከፊቷ እልፎ የቆመችበትን ወለል እያረጠበው ነው::

"ልገባ ነበር፣ እንቅልፍ ወስዶት ይሆን?"

"እንቅልፍስ አልወሰደውም ከዶክተር ጋ ስለሆነ ነው:: እህቱ ነሽ?

"እዎ፣ እህቱ ነኝ! "

" እንዴ ታዲያ ዶክተር ፋሲልን አታውቂውም እንዴ? " ትንሽ እሰበች፣

"ዶክተር ፋሲል? የት ነው የሚሠራው?"

"እዚሁ ባልቻ! ወንድምሽንም ዘመዴ ነው ተንከባከቡልኝ ብሎን እንደ እንቁላል እየተንከባከብነው ነው:: አሁንም እያከመው ሳይሆን እየተጫወቱ ነው:: ለማንኛውም ሌላ ክፍል ያሉትን ታካሚዎች አየት አየት አድርጌ እመለሳለሁ:: ትንሽ ጠብቂና ዶ/ር ፋሲል የማይወጣ ከሆነ እንኳኪና ግቢ" ብላት ዞር ስትል ወ/ሮ አረጋሽ የሚጫወቱትን ለመስማት ወደ በሩ ተጠግታ ለመስማት ስትሞክር በተደጋጋሚ "ማንም ምንም፣ እይነት ጥያቄ ቢጠይቅህ መልስህ ምንም አላውቅም፣ ፈጽሞ እላየሁዋቸውም፣ አላስታውስም ነው፣ እሽ!" የሚል እንደሰማች በጣቶቿ እገጯን ደገፍ አድርጋ በሰፊው እየተነፈሰች ውጥንቅጥ እለች:: የምትይዘው የምትጨብጠው ጠፋት:: ከአንድ ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሦስት አራት ጊዜ፣ 'ማንም ምንም ቢጠይቅህ ምንም አላየሁም፣ አላውቃቸውም" የሚል እጆሮዋ ላይ እንደገደል ማሚቶ እስተጋባባት::

"ጆሮዬ ነው ወይ እውነት መክብብና ዶክተሩ የሚያወሩት ነው?" እያለች ስትጨነቅ ሁኔታውን በአይኗ ለማየት



በተነገረችው መሠረት በሩን ኳኳ አድርጋ ከፈት ስታደርግ ከዶክተር ፋሲል ጋ አይን ለአይን ግጥምጥም ሲሉ እሱ የሚያውቃት፣ እሷ የማታውቀው ሰው "ጤና ይስጥልኝ፣ እንዴ ይጠብቁኝ" ብሏት ፊቱን ወደ መክብብ ዞር አድርጎ "በል እንግዲህ ሃኪም የነገረህን መርሳት የለብህም! ግቢ የእኔ እመቤት" ብሏት ጥሏቸው ወጣ:: ገና እንደተጠጋችው በጉልበቷ እወለሉ ላይ ተንበርክካ ግንባሯን አልጋው ላይ ደፍታ ስቅ ሰቅ እያለች "እንኳን ተረፍክ፣ እንኳን ተረፍክ የኔ ወንድም እያለች ቀስ ብላ ገለጥ አድርጋ ቁስሉን እያየች "አይዞህ እንግዲህ እኔ አለሁልህ" እያለች ነርሷ በድንገት ስትገባ የወ/ሮ አረጋሽን ሁኔታ አይታ በመደንገጥ "ኧረ ተይ የእኔ እህት እንደዚህ አትሁኝ፣ ሞትስ እስ አይደለም እንዴ፣ በቃሽ የኔ ቆንጆ ብላ እጇን ጎትታ እስነስታ ሳብ አድርጋ እቅፍ አድርጋ ጀርባዋን እሽት እሽት እያደረገች አይዞሽ በርታ በይ! ዶ/ር ፋሲል ምን ያህል ቀላል እንደሆነ አልነገረሽም እንዴ!"

"እይ ነግሮኛል፣ እኔ እኮ የሚያስለቅሰኝ የልጁ ታሪክና በቤቱ ውስጥ ያለ ጣጣ" ብላ ሳትጨርስ እንባዋን መቆጣጠር አቅቷት ፊንድቆ መውረድ ሲጀምር ነርሷ ደንግጣ ዶ/ር ፋሲልን ፍለጋ ሮጣ ወጣች::

"እኔ እኮ በጣም ደህና ነኝ:: ዶ/ር ፋሲል ትንሽ ቀን ቆይ ብለውኝ ነው እንጅ:: ከተፈቀደልኝ አሁንም እብረን መሄድ እንችላለን" ሲል ወ/ሮ አረጋሽ በድንገት"ዶ/ር ፋሲል ስመሆኑ ማን ነው? ከዚህ በፊት ታውቀዋለህ እንዴ?"

"ዶ/ር ፋሲልማ እሁን እርስዎ ሲገቡ ..." ብሎ መናገር ሲጀምር ወ/ሮ አረጋሽ በማቋረጥ "መክብብ ይሀን እንቱታ ተው ብዬህ እልነበረም!" እለችው::
"ወይ እትዬ ይቅርታ እረስቸው ነው:: እና ዶ/ር ፋሲል አንቺ ስትገቢ የወጣው ነው:: ስለመተዋወቅ ግን..." ብሎ መናገር እንዳልፈለገ እያስታወቀበት በግራ እጁ የጆሮውን እካባቢ ሳይበላው እከክ እከክ እደረገ:: ብዙም ልታስጨንቀው ባለመፈለጓ፣ አቋረጠችውና "መክብብ ቆይ ፍራፍሬ ይዠ መጣሁ" ብላ ወጥታ እገረ መንገዷን 'ዶ/ር እስክሰታ' ጋ ደውላ ስለሁኔታው እስረድታው ስለ ዶ/ር ፋሲልም ስትነግረው ማወቅ የሚገባትን ያሀል ስለነገራት በጣም ተገርማ "ሆሆይ እስር ቤት ማሰቃያ ብቻ ሳይሆን ትምህርትም እስተምሮ ያስወጣል ለካ! የሚገርም እኮ ነው:: እስራኤሎችን ያጎበዛቸውና ያስተማራቸው ስደት ሆኖ ሳለ፣ ኢሕእፓዎችን ግርፋትና እስር ቤት ብቻ ..." ትልና ዋጥ ታደርገዋለች:: የሆስፒታሉ በር ጠባቂ ወዴት ነው የኔ እመቤት ሲላት ከቁምእንቅልፏ ነቃች::
ነርሷ ወደ መክብብ ተመልሳ "ወይ እህትህ የት ሄደች? "
"ፍራፍሬ ልትገዛልኝ ነው::"
"እኔ የምለው ዶ/ር ፋሲልና እህትህ እንዴት ሳይተዋወቁ ቻሉ?" ብላ በጥያቄ ስታጣድፈው መክብብም ዐይን ዐይኗን እያየ በግራእጁጆሮውን እያሻሸ ወ/ሮ አረጋሽ እንኳኩታ ገባች::
"ምንእስቸገረሽ እሱ ይብላልን እንጅ እዚሀስ ምን ጠፍቶ ብለሽ ነው የተሸከምሽው!"
"አይ ደስ እንዲለኝ ብየ ነው::"
"በሉ ተጫወቱ ብላቸው ወጣች::



አረጋሽ መክብብ ጋ እንደተቀመጠች የዶ/ር ፋሲልንናየመክብብንዝምድናን ለማወቅ ጊዜ አልወሰደባትም:: እሷም እንደ ዶ/ር ፋሲል መካሪ ሆነች:: "ስማ መክብብ፣ ገብረብሩክ ባለፈው እንደነገርኩህ በምንም ታእምር ስለአባትህ አሟሟት ማወቅ የለበትም:: ከሌላ ቦታ እንኳ ሰምቶ ቢጠይቅህ ስለ አሟሟቱ፣ እናትህ ምንም የነገረችህ ነገር እንደሌለ መመለስ እንዳለብህ ሁልጊዜ አስታውስ::" እሽታም፣ ዛቻም በሚመስል አንገቱን ነቀነቀ::

እነ ገብረብሩክ ውይይታቸውንገና እልጨረሱም::
"የልጅቷስ ነገር መጨረሻው ምንድን ነው?" ይላል እንዱ፤
"የትርሲትን ነገርማ ያው እንደተነጋገርነው ከጣልናት ቦታ አንስቶ ለሷ ያዘነ በመምሰል ወደ ደላላው ቤት ውሰዷት::"
ደላላው በእዘኔታ እስመስሎ ወደ እረብ አገር እንደሚልካት ነው ባጭሩ ቅንብራችን የሚመስለው::"
"ጥሩ ይመስላል:: ለማንኛውም የቧን ሁኔታ ስመነጋገር ጊዜ አለን:: እሁን የሚያጣድፈን መክብብ ነጭ ለባሾቹን ያውቃል እያውቅም ነው" ተባብለው ፈገግ ፈገግ ተባባሉ::
ዶ/ር ፋሲል በድንገት በሩን ከፍት እድርጎ ሲገባ ሁለቱም ጸጥ ረጭ ብለው ሲያገኛቸው ተገርሞ "ሃይ ፋሲል! እባላለሁ" ብሎ እጁን ዘረጋላት:: ከመቀመጫዋ እየተነሳች "እረጋሽ" ብላ አጠፌታውን በፈገግታ መለሰችለት::

"እንዴት ነው ይኽ ጎረምሳ፣ ምን ሆንኩ ነው የሚለው" ብሎ ቀልድ ሊጀምር "አይ እንቅልፍ ነው" ስትለው፣ መክብብ ግን ፊቱን በእንሶላ ሸፍኖ ነፈሰ ጡሯን ትርሲትን እያስታወሰ እንባው ጆሮውን ሞልቶ ፈሶ እንሶላውን ውሃ የተደፋበት

እስመስሎታል:: በበሽታላይ በሽታ! ባልቻ ሆስፒታል ከነባ ጀምሮ ነርሶቹ፣ የጽዳት ሠራተኞቹ፣ መዝገብ ቤቶቹ፣ ብ// ምኑ ቅጣቸው፣ የሚንሾካሾኩትና የሚያናፍሉት ይዘገንነዋልም:: ትርሲትን እረዳበታለሁም ብሎም እንደመጽናናት ያደርገዋል:: ሲስተር ከበቡሽ "ዶ/ር ፋሲል ቶሎ በል የሚቀጥለው ክፍል" ብላ ሮጣ ተመለሰች:: ብዙም ሳትቆይ ወደ መክብብ ክፍል መጣችና "ሆይ ሆይ የዘንድሮ ወላጅ መጥኔውን ይሰጠው! ልጆቹ ገና መሬት ሳይለቁ እግራቸውን እያነሱ ወላጅ አነሱን መሸከም እያቃተው እነሱ ደግሞ ተጨማሪ ሸክም ያመጡለታል:: እህ እቴ 'ወላጅ መጥኔውን ይሰጠው!'"

"ምነው ሲስተር የተበሳጨሽ ትመስያለሽ?" አለች ወ/ሮ አረጋሽ::

"ለምን አልበሳጭ! የኛ ሥራ ሰማችን ብቻ ነው የሚያምረው:: ምን የማናየው ጉድ አለ ብለሽ ነው:: በተለይ ባልቻ ሆስፒታል 'ጽንስ ማሰወጣት ብሎ ጣጣ የሴቶቹ ብልግና ከከንፈር አልፈው እግር ወደማንሳት፣ አቅምን አለማወቅ፣ ወይ አምላኬ! አደራህን ሴት አትሰጠኝ" ሰትል ወ/ሮ አረጋሽ ሃሳቧን በመደገፍ አየቀለደችባት "ለዚህ ነዋ ህንድ አገር ሴት ከተወለደች ገና ከእናቷ ማህጸን እንደወጣች አፍነው የሚገድሉት::"

"እ..እ.. ህንዶች አፍነው የሚገድሉት መጥፎ ባህል ስላላቸው እድጋ ትባልግብናለች ብለው አይደለም:: አንዳንድ የህንድ ጎሳዎች ሴት ልጅ አድጋ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ ለሚያገባት ሰው ሀብት ኖራትም አልኖራትም መስጠት ያለባቸው:: ሰጠታዎች አሉ:: ያን ሰጦታ ማቅረብ ያልቻለች እሷ ብቻ ሳትሆን ቤተሰቧ ሁሉ የሃፍረትና የውርደት ካባ ነው



የሚከናነበው:: ያን በመፍራት ብቻ ነው ገና በለጋነታቸው የሚቀጯቸው:: የእኛ ጉዶች ግን ራሳቸውን እንኳን እስከሚችሉ፣ ትምህርታችን ቢያንስ በሀገራችን የተፈቀደላቸውን እስከሚጨርሱ አያስችላቸውም:: ይህ የግዜር ቁጣ ነው:: ባለጌዎች" ሰትል መክብብ ይህ ሁሉ ውርጅብኝ በትርሲት ላይ መስሎት በድንገት በተከናነበበት እንሰላ በእንባ የጨቀየ ህይኑን እየጠራረገ "ሲስተር እኔ ካንች አላውቅምና ሲቶች፣ በተለይ ትንንሾቹ የሚያረግዙት ወደው ሳይሆን በጉልበተኛ ወይም በትልቅ ሰው ታፍነው ተገደው በመደፈር ሊያረግዙ ይችላሉ" እያለ እንባውን መቆጣጠር አቃተውና እንደገና ሽፍንፍን አለ::

ለመጀመሪያ ጊዜ መክብብ ፈጽሞ ሌላ ሰው፣ የተማረ፣ የተመራመረ ሊቅ ሆኖ ታያት:: በአነጋገሩ እሷ ብቻ ሳትሆን ሲስተር ከበቡሽም ሃፍረት ይሆን መናደድ ሳይታወቅባት በድንገት ውልቅ ብላ ወጣች::

ወ/ሮ አረጋሽ ነገሩ ከነከናት:: በተለይ ከመክብብ አፍ ይህ መውጣቱ፣ የአይኖቹ በእንባ መጨቀየት፣ ሊናገረው ያልፈለገው አምቅ ሚሰጥር በልቡ ውሰጥ እንዳለ በግልጽ ማስታወቁ የመሳሰሉት ለቀጣይ ጥያቄ እያዘጋጇት ነው:: በድንገት የተከናነበውን ገለጥ ስታደርገው፣ አሁንም እንባው በግራና በቀኝ ይፈሳል:: "ትርሲት እንባዬ ወረደ፣ ከብለል ከብለል አለ" ብሎ እንደ ማጥም ነገር ቤት ሙሾ ሲያለሳስልነበር ገለጥ ያደረገችው:: "ተው እንጅ መክብብ፣ እኔንም አታስጨንቀኝ:: ምነው እለሁልህ ብዬህ የለ እንዴ? ደግሞስ እንኳንለቤተሰቦችህ አተረፌህ እንጅ ከዚህ የባሰ አለ

አይደሰም? ነው ወይስ ህመሙ እየተሰማህ ነው እንዲህ የምትሆነው?" እያለች ገና ሳትጨርስ ልክ ያበጠው ይፈንዳ በሚመስል አነጋገር "አትዬ እኔ ጤናዬ ደህና ነው። የትርሲት ነገር ግን ተድበስብሶ አይቅር... ጋሼ እስክ ወንጅ ..ወ..ወ..." እያለ ሌላ ክፍል እስከሚለማ የፀጥታ እንባው ወደ ጩኸት ተቀየረ፤ የለቅቃ እንባ።

"ኧረ በፈጠረህ አንተ ልጅ እለተ ረጋ በል፤ ግልጽ አድርገህ አስረዳኝ።"

"አትዬ ካንቺማ የምደብቀው ምንም ነገር አይኖረኝም። እስከዚያው ግን ማንም ሰው ቢጠይቅሽ ከህመሜ ሌላ ምንም ነገር የተነጋገርነው እንደሌለ መንገርሽን አትርሽ" አለ። የመክብብ ከወትሮው በተለየ ትእዛዝ አዘል አነጋገሩ አያስገረማት "እኮ የትርሲት ነገር ምንድን ነው? ለመሆኑ የት እንዳለች፣ የት እንደተወሰደችስ የምታውቀው ነገር ይኖር ይሆን? ካለ ሳንዘገይ እንድንደርስላት" ብላ ጸጥ አለች። ጸጥታው በሁለቱም በኩል ነገሰ።

ብዙም ሳትቆይ በረዥሙተንፍሳ "እረ በፈጠረህ አንተ ልጅ እኔንም አታስጨንቀኝ! ጋሼ እኮ ብለህ ጸጥ አልክ። የገብረብሩክን ስም በምን አነሳኸው?" እያለቼ በጥያቄ ስታዋክበው፣ መክብብም ላፈንጻው አላፈንጻው እያለ ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ እየተገላበጠ ሲያመነታና ቁና ቁና ሲተነፍስ ሲለተር ከበቡሽ በድንገት በሩን እየከፈተች፣ "እየሽ ወ/ሮ አረጋሽ ፍጡር የሆነ ሁሉ መክበር አለበት። መክበር ስልሽ አነጋገሩ፣ አለተሳሰቡ ሁሉ ማለቴ ነው። የሚገርምሽ ይህ ወጣት ቅድም የተናገረው በጣሙን አድርጎ ነው ራሴንየመታኝ። እኔ



በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነበር ያየሁት። እናም የተናገረው ፈጽሞ ትክክል ነው። አቦ አንተስ እግዜር ይማርህ!" ብላ ገለጥ አደረገችውና በል ንቃ በል አለቺው። ጨዋታዋን በመቀጠል ባይገርማችሁ ቅድም ከነገርኳችሁ ሌላው የሚገርመው መክብብ እንዳለው ስንት ጉድ መስላችሁ በአገራችን በምድረ ኢትዮጵያ የሚከናወነው። ስንቱ ነው የሚስቱን እህት፣ የእንጀራ ልጁን፣ የቤት ሠራተኛውን፣ ችግረኛ ሴት ልጆችን ላላድግ ብሎ ክፍ ሲሉ አስገድዶ የሚደፍር! ብቻ ምኑ ቅጡ ቤቱ ይቆጠረው" እያለች ስታነበንብ ወ/ሮ አረጋሽ አነጋገሯ ቢጥማትም ካጠገቧ ዞር ብላላት መክብብ መክብብ "የትርሲት ነገር ኮ ...ግን ጋሼ እኮ" ያላት ለምንእንደሆነ እንደምንም ተማጽና ከመክብብ ለመስማት ልቧ ድው ድው እያለ እንደ ማቁነጥነጥም እያደረጋት የለውነቷ እንቅስቃሴ፣ "ሲስተርዬ ተይኝ፣ ዞር በይልኝ፣ መስማት አልፈልግም" እያስኛት ነው።

ይግረምሽ ብሎ ዶ/ር ፋሲል በድንገት ገባና ይቅርታ እንዴ እውጭ ቆዩልኝ፣ ከመውጣቴ በፊት እየት ላድርገው ብዬ ነው። ሲለተር ከበቡሽ ሳታገኝኝ እንዳትወጭ እፈልግሻለሁ" ብሎ ሲወጡለት.... ምርመራውንቀጠለ።

"ታዲያስ አባክህ በልቀና፣ በል እንጻልኩህ ብቻህን ስትሆን በርህን ዘግተህ ግራቀኝ፣ ቁጭ ብድግ፣ ፑሽ አፕ የመሳሰሉትን ስፖርቶች አትርሳ። ለው ሲመጣ ልክ ከመታጠቢያ ቤት እንደተመለስክ ሆነህ ጥቅልል ብለህ ማቃስት ነው።" ብሎት ጀርባውን መታ መታ እያደረገው ፈገግ አለ። "ሌላው" አለው ክንድና ክንዱን ጠበቅ አድርጎ በመያዝ፣ ህይኖቹን ህይኖቹ ላይ ተክሎ "የደህንነት አባላቶች ናቸው የተባሉ በዚህ ሆስፒታል

ውስጥ በድብደባ ወንጀል የተፈጸመበት ሰው ስለተኛ ለጥያቄ እንፈልገዋለን ብለው ጥያቄ ስላቀረቡ ላንተ ለማስረዳት ጊዜ እንዲኖረኝ ብዬ የወሰድከው መድሃኒት የሚያስተኛ ስለሆነ ብለን ለነገ ቀጥረናቸዋል:: ስለዚህ ፈጽሞ እንደማታስታውሳቸው ይሁን፤ እሺ!" ብሎ ሳይጨርስ ጭንቅላቱን ነቅንቆ ክንዱን ለቀቀው:: "ደህና እደር"፡ ካለው በሁዋላ "እዚህ ሆስፒታል የምታውቀው ሰው አለህ እንዴ?" ሲለው መክብብ "አረ ፈጽሞ የለም" በሚል አይነት ጭንቅላቱን እየነቀነቀ "እእ" ሲለው ዶ/ር ፋሲል "ጉድ ጅብ!" ብሎት በሩንዘጋ::

"ይቅርታ ወ/ሮ አረጋሽ አስወጣሁዋችሁ:: በይ እንግዲህ ደህና እደሪ:: የሰጠሁት መድሃኒት የሚያስተኛ ስለሆነ ነገ ካልሆነ ዛሬ ልታገኚው አትችይም" ሲላት "አረ ምንም አይደል ዶ/ር ሥራ አይደለም እንዴ!" ስትል መለሰች::

የሲስተር ከበቡሽን ክንድ ጎተት እያደረገ በምን ዘዴ እንደሚነግራት ካሰላሰለ በሁዋላ ባይገርምሽ ያቺ ማነች ሰሚ፣ ጣ? ሰሚ ጠፋብኝ ሰማንኛውም ምን እንዳለችኝ ታውቂያለሽ፣ ያ 484 የተኛው ዘመድህ ተሻለው እንዴ ስትለኝ እኔ ደግሞ መክብብ ዘመዴ ነው ብዬ ላንቺ መንገሬን ረስቼ የቱ ዘመዴ? ብዬ ግራ ተጋብቼ ነበር::

"ማናት እሷ? እኔ ደግሞ የዶ/ር ፋሲል ዘመድ ብዬ የተናገርኩት ለወ/ሮ አረጋሽ ብቻ ነው:: እዚህ ቤት ለማንም አልተናገርኩም:: ደግሞ ማንስ ዘመድህ እንደሆነ ቢያውቅ ምንድን ነው ጭንቁ ይህንየመሰለ ሎጋ፣ ይህን የመሰለ ብልህ አስተዋይ ልጅ፣ ግንእውነት ዘመድህ ነው እንዴ?"



"ጥያቄው ክፏ በመምጣቱ እየተደሰተ፣ ዘመዴማ ቢሆን እኔም ደስ ይለኝ ነበር፤ የሆነው ሆኖ የልጁ አኗኗር በሰው ቤት ዘበኝነት እየሠራ ስለሆነ ይህ አደጋ የደረሰበት በጣም ስላሳዘነኝ ሁላችሁም እኔን ብላችሁ እንድትንከባከቡት ብየ ነው እንጅ ዘመዴ እንኳን አይደለም፤ እንድታውቂው ብዬ ነው:: በይ ደህና እደሪ ሲለ" ብሎ ሲለያት እሷም ወደ ወ/ሮ አረጋሽ እየተመለሰች "በይ እንግዲህ ደህና እደሪ፡ ነገ ከመጣሽ እገኝሻለሁ፤ በጣም የሚደንቅሽ በጣም ሲገርመኝ የነበረው የናንተ የዶ/ር ፋሲል ግንኙነት ምንም አይነት ዝምድና እንደሌላችሁ ገና እሁንተረዳሁት" ብላ ተለየቻት::

ወ/ሮ አረጋሽ ገና ስልኳን ሲታበሩ፡ ስልኳ ሲያንቃጭል "ሃሎ" ስትል "ሃይ! ምነው ልጄ የሆስፒታሎችን ጣጣ እያወቅሽ ባልቻ ነው የተኛው ብለሽ ቁጥሩን ሳትናገሪ ስልክሽን አጥፍተሽ ጠፍተሽ ዋልሽ"

"ምነው ገብረብሩክ፡ እንዲያው ዝም ብለህ እኔ ለሰው ሰው ምን አገባኝ እርፌ ሥራዬን ልሥራ ብዬ ነው ካላልክ እሁን ማን ይሙት አንተ ባልቻ ሆስፒታል አላስገባ ብለውህ ነው? ምነው ልጄ እሁንስ እንደ ህጻን እያየኸኝ ነው ያለኸው መታወቂያ ስሌላው ህዝብ የተከለከለበት ቦታ ሁሉ እንደሚያስገቡህ ሰንቴ ነው የነገርከኝ? እትርሳ እንጂ ገብረብሩክ! ለማንኛውም እቤት እንጫወታለን" ብላ ቁልኩ ተዘጋና ስለ ሲስተር ከበቡሽ ማሰላሰል ያዘች:: "ዶ/ር ፋሲል ዘመዳችሁ እንዳልሆነ አረጋገጥኩ" ያለቻት፤ ክንዷን ጎተት ያደረጋት ጊዜ እንደነገራት ጠርጥራለች:: "ግን ለምን?" እሱ ነው ያሳለባት:: ልክ አጠገቧ ላለ ሰው እንደምትናገር "ሆይ ሆይ! ውጥንቅጡ የወጣ ነገር!

እንዳለች ብቻዋን መሆኗን ስታውቅ ክው አለችና "ለሁሉም ዝምታን ነው መምረጥ" ብላ ወሰነች::

"ወይኔ እናቴ፣ ኧረ ስለእግዚአብሄር ፣ ኧረ በእናታችሁ እንዲህ አታድርጉኝ፣ ምነው ሴት እህት የላችሁም፣ እሆዴ ውስጥ ጽንስ እስእከ እባካችሁ አታጉላሉኝ" እያለች ስትለምን ሰአረመኔው እፋኝ የትርሲት መማጸን ልክ የሰደበችው መስሎት ይባሱን በመናደድ "ጽንስ? በይ ነይ ውረጂ" ለመሆኑ ከማን ነው የጸነሽው? ልብብሎ ሳዳመጠውና አተኩሮ ሳየው ማርገዟን ቀደም ብሎ እንደሚያውቅ እያስታወቀበት "ብትናገሪ ይሻሏሻል አንገትሽን ሳልጠመዝዘው!" ሲላት "ስለ ማላውቀው ነው" ብላ ገና ተናግራ ሳትጨርስ "መቀለዱ ነው!" ብሎ በዚያ በቆረፈደ እጁ ፊቷንይ በጥፊ ፍም አስመሰለው:: ያለ የሌለ አቅሟን ተጠቅማ ጩኸቷን ለቀቀችው:: ለካስ ለመጮኸም ጉልበት ያስፈልግ ኖሯል፣ ጩኸቷ ብዙም እልተሰማ:: ትርሲት ጩኸቷ መና ሆኖ ቀረ:: "እሪበከንቱ" እንባዋን እያዘራች ፊቷን እያሻሸች "ቅደሚ!" ተብላ ጸጥ ረጭ ብሎ ወፍ እንኳ ዝር በማይልበት ሰፈር፣ ከፊት ከፊት ያቅሟን ያክል እየዳከረች ነው:: ዱላውም ረሃቡም፣ ውሃጥሙም፣ ነፍሰ ጡርነቱም ተደማምረው ትርሲት በጣም ተዳከማለች:: መራመድ አቅቷት ፍጥነቷ ሲቀንስ በድንገት በያዘው የከዘራ ዱላ "ፈጠን በይ አንቺ" ብሎ ገፋ ሲያደርጋት ተግግተርትራ በጉልበቷ በርከክ ስትል "በይ ቀልዱን ተይና" ብሎ ከሌታዋን በእጁ ጎተት ሲያደርጋት ትርሲት እንደ ትርሲት መሆኗ አበቃ:: ትዕግስቷ ተሟጠጠ፣ "በቃ ግደለኝ" ብላ የግራ እጁን ጣት በንክሻ እንደ አንበሳ ቆረጠመችለት:: በያዘው ከዘራ ዱላ በቀኝ እጁ ጆርባ



ጆርባዋን ይላታል:: ትርሲት እንደተራበ ነብር ጣቱን ይዛ "እም እም" ትላለች:: ዱላውም አላቆመም:: ከጭንቅላቷ ላይ ደም ሲፈነጠቅ"እ..እ" አለችና ሳትገላበጥ እግሮቿና እጆቿ ሰው እንዳስተካከላቸው ሆነው ተዘረጉና ድፍት አለች::

"እንተ ብዙ ነገር እያበላሽህ እኮ ነው፣ ምንድነው ለሴት ልጅ እንዲህ የሚያደርግህ" ሲለው "ጣቴን አየኸው፣ ይች ውሻ ሰብራዋለች እኮ" ብሎ በወደቀችበት በዚያ በከዘራው ራሷን ለመምታት ሲሰነዝር እንደምንም ታግሰው ከዘራውን ነጠቁት::

"በሉ የምናደርገውን እናድርግና ሃኪም ቤት ውሰዱኝ:: ጥርስ መርዝነት ስላለው ሌላ ችግር እንዳያመጣብኝ" ሲል ሌላኛው ትርሲትን እጇንይዞ ቀናይ ሲያደርጋት ሲሞክር በድንሀናለች:: እጇን ሲለቀው እንደ እቃ ዘፍ አለ:: "በቃን የልጅቷ ሚሽን እዚህ ላይ ያበቃል! እክትሞላታል:: ይልቁንስ ዱርዬ እንዳበላሻት ለማስመሰል ሰዓቷንና አንገቷ ላይ ያለውን ወርቅ እናውልቅና እዚህ አካባቢ ቶሎ ዞር እንበል" ሲል አሳሰባቸው:: እንዳሉትም ዱርዬ የዘረፏትን የደፈራት እንዲመስል አስመስለው ከመንገዱ ወደ ዳር ጎተት አድርገው ጥለዋት መኪናቸውን ወዳቆሙበት ተፍ ተፍ እያሉ ተመለሱ:: ትርሲትም በኮረኮንች መንገድ ላይ ሳይቆረቁራት ጸጥ ረጭ ብላ ድፍት ብላዋለች:: መኪናቸው እካባቢ ሲደርሱ ንትርካቸው ከመብዛቱ የተነሳ የሚደማመጡም አይመስሉም:: እንዱ ይደስታል፣ እንዱ ይቆጣል፣ ሌላኛው "ምን ይባላል፣ ለገብረብሩክ ምን ይነገራል" ይባባላሉ:: የተሰበረች ጣቱን ሰብቻዋ ቀስሮ "እሱን ለኔ ተውት ለገብረብሩክ እንደሚገባው አድርጌ እነግረዋለሁ" ብሎ ወደ ገብረብሩክ ይደውላል::

"ሃሎ! ገብረብሩክ"

"ሃይ! ታዲያስ ድምጻችሁ ጠፋክ!"

"አይ፣ ብንጠፋም ለጥሩ ነገር ነው!"

"እንዳሰባችሁትና በተነጋገርነው መሠረት አደረጋችሁ?"

"በሚገባ! እንዲያውም በተሻለ መንገድ!"

"ደግሞ ከምን ጊዜው የተሻለ መንገድ አገኘችሁ!"

"ባጭሩ ለመጠረዝ፣ ከተዘጋጁት ሰዎች ጋ እንድትደባለቅ ሆኗል። ነገ ወይም ዛሬ ለሊቱን ይሄዳሉ። የአረቡ አገር ጉዞ ተሳካ አልተሳካ አያልን ከምንስጋ ባጭሩ እንገላገል ብለን ነው።"

"እሱስ ጥሩ ነበር፣ ይህን ቅንብር ቀደም ብላችሁ ለኔ ሳትነግሩኝ ማለቴ ነው እንጂ።"

"ያንተ አባባልማ ይገባናል፣ ግን ይሄ ሁኔታ ባጋጣሚ የሆነ ነው። ሎተሪ እንደወጣልን ቁጠረው!"

"በጣም ጥሩነው። ለቀጣዩ ጉዳይ ሌላ ተጨማሪ ሰውም አዘጋጅቻለሁ። ከነገ ጀምሮ እንደተመቻቸው ባልቻ ሆስፒታል ሄደው መክብብን ቃለ መጠይቅ ያደርጉለታል። "ለማንኛውም እንደዋወል። ደህና እደሩ።"

የባልቻ ሆስፒታል የውጭ በር እንደሁልጊዜው በጠያቂ ጭንቅንቅ ብሏል። የዛረው ደግሞ ከመቻውምለየት ያለ ነው። በር ላይ ቆሞ ግባ አትግባለሚለው ሰውየ እንኳን ማር ለማለስ፣ መጨበጥ እንኳ አልተቻለም። ጠያቂው መፍትሄ የሆነመሰሉት ይጉረመረማል። አንዳንዱ "ሆሆይ! የባልቻ ሆስፒታል አለማስተኛት ሥራ የለውም እንዴ? ባይገርማችሁ የኔ ወንድም ከትናንት በስቲያ ጉንፋንቢጤ አመመኝ ዶ/ር ባይ ይሻላል አሁን አመለሳለሁ ብሎ ብቻውን እሽክም እያለ መጥቶ "አደገኛ ሁኔታ ነው መተኛት አለብህ ተብዬ ተኝቻለሁ" ብሎ ደወለልን" እያል ሰገና ሳይጨርስ፣ ከወደ ግራ በኩል ከበሩ አጠገብ ቆመው ለመግባት ካሰፈሰፉት መካከል አንዷት ሴት ወ/ሮ "ስማህ የኔ ወንድም፣ እዚህ ቤት ብዙ ጉድ አለ። እንግዲህ ያንተ ወንድም ለቀላል በሽታ እዚህ እንዲተኛ ያደረጉት ጥሩ የህክምና ኢንሹራንስ ይኖረው ይሆናል" ሲሉት "እንዴ! አዎ፣ ያውም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው!" "እ..እ ..!" አሉና "የሚታለብ ላም የአየር መንገድ ኢንሹራንስ!" ሲሉ "አይ የእኔ እህት፣ አየር መንገዱማ ሠራተኞቹን የተንከባከበ መስሎት ነው እንጅ አለአግባብ ውጭ ማውጣት መች ፈልጎ ብለሽ" እያለች ሳለ አንድ የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሰና ሁለት ነጭ ለባሾች ገና እበር ጋ ሊደርሱ ዘበኛው ተደውሎ በተነገረው መሠረት ሰላምታ ሰጥቶ አስገባቸው። በተለይ የፖሊስ ልብስ የለበሰውን ፖሊስ ሌላፖሊስ "ምንድን ነህ አንተ ደግሞ ምን ታደርጋለህ፣ እንዴት እዚህ ልትገባ ቻልክ የማናውቅህ መሰለህ፣ ሞላጫ ሲባ፣ እጅ ወላይ" የሚባል ምስሎት አረማመዱ፣ አተነፋፈሱ፣ አስተያየቱ ብቻ ምኑ ቅጡ ሁሉ ነገሩ ይንቀገርቀገርል።

ገና መዝገብ ቤት እንደደረሰ በማስተናገድ ላይ ያለችዋን ወጣት ሰላምታ እንኳ ሳያቀርብላት "ከማእከላዊ ነን፣ መክብብ ታምራት ስንት ቁጥር ነው?" ሲል ጠየቃት። ቀደም ብሎ ስለተነገራት ብዙም አልተደናገጠች። "484 ነው ጊታዬ" አለችው። በስክንዶች ውስጥ ከመክብብ ክፍል ደረሱ። ክፍሉን ቀስ አድርጎ ከፈት ሲያደርገው፣ ሲስተር ከበቡሽ እቃወቿን እያሰባሰበች ሳለች፣ "ይቅርታ የእኔ እመቤት ሥራሽን ጨርሰሽ

ከሆነ ከመከላከያ ነው የመጣነው ኢቶ መክብብን ለጥያቂ ስለምንፈልገው እንዴ ብትወጭልን" ሲል ገለጸላት::
"ጨርሻለሁ ጌታዬ" ብላ ጋሬዋን እየገፋች ወጣች:: "እንኳን ተረፍክ፣ ልጅ መክብብ!" እያለ እጁን ዘረጋ፣ መለዮ ለባሹ ለመክብብ:: "ባምላካችሁ" ብሎ መክብብም እጁን ዘረጋ:: "በቀጥታ ወደመጣንበት ጉዳይ ነው የምናስገባህ" አለ እንደመቆጣት እየቃጣው:: ""ምነው ደህናም አይደላችሁ እንዴ?" አለ ማወቁ እንዳይታወቅበት እየተጠነቀቀ:: "ደህናማ ሆነን ነው አንተን ለመርዳት የመጣነው" ብሎ ድርቅ ያለ የውሸት ፈገግታውን አሳየው:: መክብብ ሀይኑን በሀይኑ ላይ ተክሎ መናደድ ይሁን በሃሳብ መዋጥ በማያስታውቅ መልኩ ፀጥ አለ:: ቁስሉ ገና ስላልሻረለት አርር ብግን ብሎ ልቡ ደው ደው እያለ በሰኮንዶች ውስጥ ላብ አጠመቀው:: "ምነው ደነገጥክ እንዴ? አይዞህ መንግሥት ምኔም ለተበዳይ የቆመ መሆኑን አትዘንጋ! ካንተ የምንፈልገው ስላጋጠመህ ሁኔታ ምንም ሳትደብቅ በዝርዝር እንድትነግረን ነው:: በተለይም አደጋውን ያደረሱብህን ምስላቸውን በሚገባ እንድትነግረን ካሁኗ ደቂቃ ጀምረህ ተዘጋጅ:: ሰዎቹን በግልጽ ነግረኸን በቁጥጥር ሥር ካላዋልናቸው አረሳስተው የከፋ ችግር ሊያደርሱብህ ይችላሉ:: በጭሩ መንግሥት ከፍተኛወጭናብዙ ጊዜ የሚያባክነው አንተን ለማገዝና ጠላቶችህን ወይም ወንጀለኞችን ለፍርድ ለማቅረብ ነው::

መክብብ አሁንም ሀይኑን አሰውየው ላይ እንደተከለ "የሌባ ሀይን ደረቅ መንግሥት እናንተኑ ለማፈላለግ ለምን ጊዜናገንዘብ ያባክናል፣ ሌቦቹ፣ አጭበርባሪዎቹ፣ ነፍስ ገዳዮቹ፣



ይኸውከፊቴ ቆማችሁ የለ እንዴ? ግለሰቦችን በአጭር ጊዜ ማታለል፣ ማጉላላት፣ መዝረፍ ትችሉ ይሆናል፣ መንግሥትን ያክል ነገር ግን ልትቀልዱበት አትችሉም:: አሁን ምንም ጊዜያችሁን ሳታጠፉ ሁላችሁም እግዜር በኪነ ጥበቡ ለኔ ሃይልናሥልጣን የሰጠኝ መሆኑን አውቃችሁ እጃችሁን ወደ ላይ! እንዳትበላሹ ነግሬያለሁ! እንዳትበላሹ" ብሎ ሃሳቡን ሳይጨርስ በላብ እንደተጠመቀ "እ..እ .. እም እም" ብሎ በሰፊው ማቃሰት ሲጀምር ድንግጥግጣቸው ወጣና አንደኛው በሩን ከፍቶ "ሲስተር ሲስተር" ብሎ ሲጣራ ሲስተር ከበቡሽ ከሚቀጥለው ክፍል ሮጣ ስትገባ እነሱም ከበውታል፣ መክብብ ያቃስታል::

ገና ሲስተር ከበቡሽን ሲያያት እንደምንም ተንጠራርቶ ያለ የሌለ ሃይሉንተጠቅሞ ነጩን ኮቷን ጭምድድ አድርጎ የ ቻለውን ያክል ወደእጠገቡ ጎትቷት አንገቱን ቀና አድርጎ በእጁ የጨመደደው ኮቷ ላይ ድፍት አድርጎ ማቃሰቱንቀጠለ:: "እርጅኝ ሲስተር፣ እርጂኝ የእኔ እህት ከዚህ ጉድ አውጭኝ፣ እነዚህን ጭራቆች እፊቴ ዞር አድርጊልኝ ሲስትርዬ፣ ስለወንድ ልጅ አምላክ ብለሽ አድኚኝ" እያለ ልብሷን እንደያዘ በሃሳቡ ሲብከነከን፤
እንደምንም ብላ "አይዞህ የእኔ ወንድም" ብላ እንደምንም ቀና ስታደርገው አተነፋፈሱ ስላላማራት፣ ይቅርታ ወንድሞቼ ሳያመው የቀረ አይመስለኝም:: ዶ/ር ከመጥራቴ በፊት መሥራት ያለብኝን ልሥራ እባካችሁ እንዴ እውጭ ጠብቁ" አለች:: ጊዜም ሳታባክን የደም ግፊቱን፣ የልብ ትርታውን፣ አዳምጣ ከመዘገበች በሁዋላ፣ የመሮጥ ያክል እየፈጠነች ዶ/ር

ፋሲል አለበት ክፍል እንደገባች "ዶ/ር ፋሲል !" ብላ የምርመራውን ውጤት ስታሳየው ዋው! ብሎ በፍጥነት እየተራመደ ሊገባ የበሩን እጀታ ያዝ አድርጎ ሊገባ ሲል፣ መለዮ ለባሹ "ይቅርታ ዶ/ር ከመክብብ ጋር ያለንንጉዳይ ገና አልጨረስንም ነበር:: ምን ያክልእንደሚያቆይህ ልትነግረን ትችላለህ?" ሲለው፤

ዶ/ር ፋሲል "እ..እ.." ብሎ ንዴቱን ለመዋጥ እየሞከረ ግን መናደዱ እያስታወቀበት ፊቱን ሙሉ በሙሉ ወደነሱ ዞር በማድረግ "ሰላም ዶ/ር ፋሲል እባላለሁ:: የመክብብን ጤንነት በቅርብ ለመከታተል የተመደብኩት እኔ ነኝ:: ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ? ማለቴ ዘመዶቹ፣ ጓደኞቹ? እያለ ፈገግ ሲል ሌላኛው መርማሪ ተብዬ የመለዮ ለባሹን አጠያየቅ በማናናቅ፤ "ይቅርታ ዶ/ር ይህ ጎረምሳ አዲስ ጓዳችን ነው:: ማንነታችንን ግልጽ ለማድረግ ያክል ከማእከላዊ መሥሪያ ቤት መክብብ ስለደረሰበት አደጋ፤ ከአንደበቱ ለመስማት ተልከን ነው" ብሎ በላስቲክ የተሸፈነች መታወቂያ ዶ/ር ፋሲል ፊት ላይ ገጭ አደረገበት::

"በጣም ጥሩ ወንድሞቼ፣ ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኖልኛል:: ሁኔታውን ማየት አለብኝ" ብሎ ከፈገግታ ጋር ፊቱን አዙሮ እየገባ "አንዴ እዚሁ ጠብቁኝ፣ በ10 እና ብ15 ደቂቃ ውስጥ ስለሁኔታው እነግራችሁዋለሁ" ብሎ በሩን ግጥም አድርጎ ዘጋው::

ዶ/ር ፋሲል ገና ከመክብብ ጋር ሀይን ለሀይን ግጥምጥም ሲል፣ ቀስ ብሎ በመንሾካሾክ "ምነው፣ መክብብ? ከተነጋገርነው ውጭ ምንተፈጠረ?" ሲል ጠየቀው:: "ምንም



አዲስ ነገር የለም፤ ግን.." አለና ዝምሲል "ሃይ ነቃ በል! እንጅ፣ ብዙም ጊዜ የለንም:: እ..ግን አልክና ዝም አልክ እኮ" በማለት ዶ/ር ፋሲል መክብብ እንዲያናግረው ገፋፋው:: ""አይ ማለቴ.. ሌቦች፣ አጭበርባሪዎች መሆናቸውን በሚገባ ሳውቀውና ህይኔ ህይናቸው ላይ ሲያርፍ ብስጭቱን መዋጥና መሸፈን ስላቃተኝ ስሜቴን ለመደበቅ ስል ነው ይህን ዘዴ የተጠቀምኩት" ሲል መክብብ ለዶ/ር ፋሲል አብራራለት:: "ምነው ስንነጋገር ከርመንምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? በዚህ ሁኔታማ የትም ሳንደርስ ሜዳ ላይ መቅረታችን ነው" ብሎ ዶ/ር ፋሲል እንደመቆጣት ሲቃጣው፣ "ዶ/ርዬ" አለ መክብብ በድንገት:: "የተነጋገርነው በሙሉ አልቤ ውስጥ በክብር ተቀምጧል:: እንደዚህ አይነት አጋጣሚ ላይ የደረስኩት የፈነከተኝ ለውዬ እራሱ እኮ ነው ላንተ ነው የቆምነው፣ መንግሥት ነው የላከን፣ የለዎቹን ምስል በግልጽ ንገረን .. እያለ ሲቀባጥርብኝ ትእግስቱ አልቆ ለዚህ የበቃሁት" ብሎ ሳይጨርስ አመልካች ጣቱን አፉ ላይ አድርጎ " ቀ ስስ..." እያለው "ይገባኛል! ከዚህ የባሰም ሁኔታ ሊያጋጥምህ ይችላል:: ቲያትረኛ ስለመሆን የወሰድካቸውን አጠር አጠር ያሉ ጥናቶች በተግባር ማዋልህን ሁልጊዜ አስታውስ!! ማልቀስ ያለብህ ቦታ አንባ እንኳ አንቢ ቢልህ ለማልቀስ መታገል፣ መሳቅ ካለብህ፣ ካልቻልክ ተሟሙተህ ፈገግታ፣ ውዘተርፈ ... ገባህ? በተጨማሪ ላስታውስህ የምፈልገው፣ አባትህን ለማስታወስ ሞክር! ለምሳሌ ያክል፣ ለምን ሞተ? ስለ ሃቅ ወይም ስለ እውነት መታገል መከራከር ስትፈልግ 99 በመቶ አርበኞችን አስብ፣ የአርበኛ ልጅ አርበኛ ነው:: የሚጠቅምህን ነገር ለማግኘት መዋሸት

መቀላመድ፣ ማምታታት፣ ሲያስፈልግህ እያትህ የነገሩህን በጣሊያን ወረራ ጊዜ ፋሽስቱን ጠንካራ አርበኞቻችን ከአገራችን ካባረሩት በሁዋላ ሃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ሲመለሱ፣ ለጣሊያን ሲያጎበድዱ፣ አርበኞቻችን የመሸጉበትን ቦታ ለፋሽስቱ እየመራ ሲያስመታ የነበረ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ ባንዳ ሁሉ 'ፀሐዩ ንጉሳችን እንኳን በሰላም ተመለሱልን'በማለት ያውም ስንደቅ ዓላማ ሳይሆን ነጭ ጨርቅ አውለብልቦ በመቀበሉ ስንቱ ነው ደጃዝማች፣ ቀኛዝማች.. ብቻ ምኑ ቅጡ .. ያልዘራውን ያልኮተኮተውን፣ ያልደከመበትን ሲጠቀም የኖረው:: ባጭሩ ዋሽተህ ማግኘት የፈለከውን ለማግኘት ያግዙሃል:: የባንዳ ልጅ ባንዳ፣ የመሳሰሉትንም ቃኛቸው:: የነባላይ ዘስቀን ታሪክ ስታስታውስ ደግሞ፣ በዓላማህ የጸናህ ትሆናለህ፣ ሞትና ስቃይን ቅንጣት ታክል አትፈራትም:: እውነትን፣ ሃቅን የያዘ ሁሌ በሃይልና በድፍረት እንደተከበበ ነው!! ሁልጊዜ ከእንገቱ ቀና እንዳለ ነው የሚኖረው:: በል እንግዲህ እንዳላይ ነገርኩህ፤ እርግጠኛ ነኝ በደንብ እንደተከታተልከኝም ተስፋ አደርጋለሁ:: ለማንኛውም ማነጋገር አይችልም ብዬ ልሸኛቸው? ወይስ ምን ይመስልሃል?" ሲል ዶ/ር ፋሲል ሃላፊነትና ወኔ በተቀላቀለበት እንደበቱ እማከረው:: "እንደኔ እንደኔ ብገላገል ይሻለኛል" አለ መክብብ::

ዶ/ር ፋሲል ሀይኖቹን ከፊት ግንባሩን ጨምደድ በማድረግ "በተቻለህ መጠን ተቃራኒ መልስ ስመስጠት ሞክር:: ሁሉም ያለው እዚህ ውስጥ ነው" ብሎ ጣቶቹን በእርግብግቢቱ ላይ አድርጎ እያሳየው፣ አይዞህ፣ ጥያቄ እንዳያበዙብህ የስጠሁት መድሃኒት ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ስለሚያስተኛው ቶሎ ቶሎ



ጠይቁት እላቸዋለሁ" ብሎት ሲወጣ መክብብም ስስተቃራኒ ምንነት እያስላሰለ ጣእረ ሞት የመሰሉት ተቆርቋሪ 'አዛኝ ቂቤ እንጓች' ወዳጆቹ ገብተው ከፊቱ ተደረደሩ:: "በል እንግዲህ ካለን የጊዜ እጥረት አንጻር በቀጥታ ወደጀመርነው ጥያቄ ነው የምንሄደው::

መርማሪ "ስምህ መክብብ ታምራት ነው፣ አይደለም?"

"ልክ ነው"

"የትውልድ ቦታ?"

"ናዝሬት"

"ብሄርህ?"

"ብዙ ነው!"

"ለቀልድ ጊዜ ያለን አይመስለኝም"

"እረ እኔም የምሬን ነው:: እስቲ እራሳችሁ እስቡት የእናቴን ዘር ብነግር እባቴን ቅር ይለዋል" እያለ ለማስረዳት ሲሞክር፣ ገና ሳይጨርስ "ናዝሬት የኦሮምያ ክልል ስለሆነች እለና 'ብሄር ኦሮሞ' ብሎ መረጠለት::

"እድሜ?"

"ወደ 26"

የትምህርት ደረጃ?"

"12ኛ"

"የምትማርበት ት/ቤት ምሥራቅ እጠቃላይ"

"ሥራ?"

" እዘመድ ቤት ነው የምኖረው"

"ማለቱ፣ ምን ትሠራለህ?"

"ሁሉንም አይነት ሥራ"

"ዘመድህ ማናቸው?"

"ሁለቱም፣ እትዬም እንደ እህቴ፣ ጋሼም እንደወንድሜ ናቸው"

"ይህን የደረሰብህን አደጋ ሰምተዋል?"

"እዎን፣ እትዬ እንደያውም መጥተው ጠይቀውኛል"

"ማን ይባላሉ?"

"ወ/ሮአረጋሽ"

"ባለቤታቸውንስ"

"አቶ ገብረብሩክ"

"አቶ ገብረብሩክ ለምን ይመስልሃል ያልጠየቁህ?"

"እንዲያውም፣ እትዬ ለእርሳቸው በጣም ሲያስቡ ነበር:: እንዴት ቤቴ ተደፈረ፣ እንደ ታናሽ ወንድማቸዋን እህታቸው ስለሚያዩን በደረሰብን ሁኔታ በጣምይደነግጣል ብለው ስላሰቡ ቀለል አድጌ እንገረዋለሁ ሰላሏቸው ለዚህ ይሆናል"

"እህት አለህ እንዴ?"

"የለኝም"

"አቶ ገብረብሩክ ማንን ነው ታዲያ እንደ እህታቸው የሚያዩት?"

"እ! ትርሲትን ማለቴ ነው"

"ትርሲት ማን ናት?"

"ትርሲታም እኔን የመቱኝ ሰዎች የወሰዷት ነች"

"ልማነጋገር ያክል ነው እንጅ የቢንም ሁኔታ እየተከታተልን ነው:: ያንተም እገዛ ሊያስፈልገን ይችላል::"

"በእሽታ ራሱን ነቀነቀ"

"ለመሆኑ የት እንዳለች ታውቃለህ?"



"በጭራሽ!"

"በጣም እንገብጋቢው የቻልከውን ያክል በማስታወስ አደጋውን ያደረሱብህ ግለሰቦች ምስላቸውን፣ ልዝላቸውን፣ ..የመሳሰሉት ብትጠቁመን አሳደን ለመያዝ ይቀለናል:: ለመሆኑ ምን አይነት ሰዎች ናቸው?"

መክብብ ፀጥ ብሎ አይኑን በመክደን ቀጭኑን ወፍራም፣ ጠይሙን ቀይ ለማለት እየተዘጋጀ ሳለ፣ መርማሪው በእጁ የመክብብን ትክሻ ነቅነቅ በማድረግ "በል እይዞህ፣ ጎበዝ" ሲለው "ሰዎቹ መልካቸው ቀያይ ይመስለኛል:: ሰውነታቸው ግን ወፋፍራም ናቸው::" አለ::

"መኪናስ አላቸው?"

"መከና ይዘዋል:: ተለት ያለ መልኩ እንደ ቢጫ ቀለም ነው::"

"ምን ያህል ጊዜ እዚህ እንደምትቆይ ታውቃለህ?"

"ገና አልነገሩኝም"

"ለመሆኑ የሆስፒታሉን ውጭ ማነው የሸፈነልህ?"

ድንጋጠውን ዋጥ አድርጎ "ያጠራቀምኩት ብር አለኝ"

"ከሆስፒታል ስትወጣ የት ነው የምናገኝህ?"

መክብብ እንቅልፍ እንዳስቸገረው ዐይኑን ከደን ከፈት እያደረገ "ያው እምኖርበት" ብሎ ሳይጨርስ እንደገና ዐይኑን ከደን ሲያደርግባቸው፣ ሌላው መርማሪ፣ "አይ የሚበቃን መሰለኝ፣ ዶክተሩም እኮ የሚያስተኛ መድሃኒት ስለሰጠሁት ቶሎ ቶሎ በሉ ብሎ ተባብሮናል፣ በቃ እንሂድ፣ በል ጌታው እግዜር ይማርህ" አለው:: መክብብ የተኛ መስሎ ሌላ ጥያቄ እንዳይከተልበት ዐይኑን ክድን አድርጎ "እ..እ እ" ማለት

ጀምሯል:: መርማሪው ወደ ሌላኛው ጆሮ ጠጋ ብሎ "ጥፊዋ ዋጋ ስጥታለች፡ እየሀ ገና በደምብ ሳያየን ሀይኑ ላይ የመረከበት ጥፊ ቀይ ቢጫ ወፍራም ብቻ እንዲያይ አድርጓታል:: ሊያውቀን የሚችልበት ምንም ፍንጭ የለም:: ትልቅ ግልግል ነው!!"

አቶ ገብረብሩክ ወ/ሮ አረጋሽ እንዲህ ዓይነት ሃይለኛ ቃል ተጠቅማ ተናግራው ስለማታውቅ "ይገርማል፡ ሀጻን አደረከኝ.. ሀጻን አደረከኝ" ይላል ብቻውን እየደጋገመ:: ባልቻ ሆስፒታል የላካቸው ቀጭ በሉዎች ተነቅቶባቸው እንዴት ልትግቡ ቻላችሁ፡ ምን ለማግኘት ነው ይህንን ሀመምተኛ አላስተኛ ብላችሁ በተልካሻ ጥያቄ እረፍት የምትነሉት? ብዙ ጣጣ ውስጥ ሳትገቡ እውነቱን ከነገራችሁን ቅጣቱ ሊቀልላችሁ ይችላል፡ .. ቀጭ በሉዎቹ ከወ/ሮ አረጋሽ ጋር እዚያው ባልቻ ሆስፒታል ተያይተው እንዳታየው ሊሸሽ ሲሞክር እንዴት ሊሸሽኝ ቻለ ብላ ተከታትላ አስይዛው ይሆናል ..." እያለ በሃሳብ ይብከነከናል::

ወ/ሮ አረጋሽ እቤት ውስጥ ገብታ አተቀመጠበት ቦታ ድረስ ሂዳ "እሺ ገብረብሩክ" አለከምትለ እንደ ሃውልት ደርቆ ቀጭ ብሎ ነበረ:: ቀና ብሎ መልስ ከስጣት በሁዋላ፡ እንቅስቃሴዋን ዐይኑን አተኩሮ ይመለከታታል:: "ምነው ገብረብሩክ፡ ቀዝቀዝ አልክሳ?" አጠያየቋ ምንም ነገር ከበስተሁዋላው እንደሌለው ከተረዳ በሁዋላ በስፊው ተንፍሶ "ውይ ..የዛሬውስ ሥራ እንዴት ትንፋሽ አሳጥቶኝ ዋለ



መስለሽ? ከዚያም በተጨማሪ እውነቱን ለመናገር መክብብን ለመጠየቅ ጊዜም በማጣቴም ሃፍረት ይዞኛል::"

"አይ እየተሻለው ነው:: ብቻ ይህን ያደረጉትን እግዜር ይይላቸው:: መንግሥት ተከታትሎ ባይደርስባቸው እግዚአብሄር የሚሳነው ነገር የለም፡ እግዜር ደግሞ እንደ ሰው አይቸኩልም፡ አንድ ቀን የእጃቸውን ያገኟታል:: "

"እኔ እምልሽ፡ ለቀበሌም እንኳን አላስታወኩም እኮ" ሲል ወ/ሮ አረጋሽ እንደመደንገጥ ብላ "እንዴ! ቀበሌያችን ሳያውቅ እንዴት ፖሊስ አውቆ መክብብን ቃል መጠይቅ ሊያደርጉ መጡ?" ገብረብሩክም በተራው ክው ብሎ "አይ ማለቴ ለብዙ ጓደኞቼ ተናግሬ እነሱ ክትትል እናደርጋለን ብለውኝ ነበር ዘንግቸው ነው እንጅ!" ሲል መለሰ::

"እንዲያው ለመሆኑ የሚያገኙዋቸው ይመስልሃል?"

"መክብብ ትክክለኛ መረጃ ማለትም መልካቸውን፡ ቁመናቸውን፡ የሚነዱትን የመኪና አይነትና ታርጋውን ከሰጣቸው በሁለት ሦስት ቀን ውስጥ አገቡበት ገብተን እንይዛቸዋለን"

"እግዜር ፈጣሪ አምላክ ባደረገውና በተያዙ፡ ለምን ይህን አጸያፊ ተግባር በነዚህ ምስኪኖች ላይ፡ እኛን ብለው፡ እኛን አምነው በመኖራቸው የፈጸሙትን ሳላውቅ ብቻ እንዳይገለኝ!::

ለመሆኑ የዚህኛውስ ሁኔታ ታውቋል፡ የትርሲት ጉዳይስ የት ገብታ ይሆን?

"እኔ እኮ እንዳታስቢ ብዬ አልነገርኩሽም እንጅ አሁንየቀረኝ ነገር ቢኖር ኤርትራዊነትዋ ታውቆ ወደ አርትራ ከሚላኩት ጋር ተደባልቃ እንዳይሆንማጣራት ነው:: ለሞኑን ሥራዬን

ጥዬ እፏን ፍለጋ ስባዝን ነው የምውለው።" ሳታስጨርሰው ሁለት እጇን ወደፊት በመዘርጋት ወደ ላይና ወደ ታች በማወዛወዝ " ብሩክዬ .. ስደፋልህ ስፏስ አይድከምህ፣ ያደራ ልጆችን እኮ ነች። ነገ ጥዋት አባቷ ይመጣል፣ ምን ይባላል? በፖለቲካ እንደሆን 'የዘላለም ጠላት የዘላለም ወዳጅ የለ' መጣላት እንዳለ ሁሉ መታረቅም አለ። ትርሲት ደግሞ ኤርትራን ያው እንደደንቡ እንደ አንዱ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ነው እንጅ የምትቆጥረው እራሱንእንደቻለ አገር እንኳንስ እሷ አባቷም 'አይ ወገኖች፣ ድንቁ፣ም ባለ ነጻነት' እያለ እንዳሾፈባቸው ነው። በችኩሎች ግፊት ሲሄድ የ ቻለው፣ ከዚያ በተጨማሪ የትርሲት እናት የነጠረች የሀረር ሰው ነች። ማሰብ የሚችል ሰው ከቶ እሷን ከምድረ ኢትዮጵያ ንክች ሊያደርጋት አይችልም።

እጅግ በጣም የምትናፍቀኝ ውዷቷ እህቴ ትርሲትዬ! እንደምን አለሽልኝ? ስረዥም ጊዜ ልበለው ድምጽሽን ባለመስማቴ ስጋቴ እየጨመረ፣ ጭንቀት በጭንቀት ሆኜ፣ አሁን አሁንማ እንቅልፍ እምቢእያለኝ ተቸግሬያለሁ። ስልክ ደውዬ ሰውየውን አግኝቸው ያለኝን ብነግራሽ ፣ እንቺም እንደኔ እንዴት እንድምትስቂ ደጋግሜ ሳስብሽ ነው የከረምኩት። "ልብ እየተቃጠለ ጥርስ ብልጭ ሲል ምንኛ ቃጠሎው ይበዛል መሰለሽ? እንድታውቂው ያክል የስፈር ጎረምሳ 'ወዳ ጥላን ጠፋች' ሲል ምንም አላፈረም። የሱን ሳጥናኤላዊ ድርጊት ባልሰማ ኖሮ ምነው ትርሲትዬ ሳታማክረኝ ብዬ ቅር ይለኝ ነበር። 'ስልክ እየተሽቀዳደመ እሱ ነው የሚያነሳው' ስላልሽኝም የቻልኩትን ያክል ሞክርኩ ወ/ሮ አረጋሽን ማግኘት



አልቻልኩም። የሆነ ሆኖ ብዙ ካወጣሁና ካወረድሁ በሁዋላ ወ/ሮ አረጋሽን የማገኝበት ሁኔታ ስላገኘሁ ከሷ ጋር መገናኘታችሁ አይቀርም ብዬ ነው ይህን ደብዳቤ የጻፍኩልሽ።

ትርሲትዬ፣ ጽንሱን በተመለከተ ካሁን በሁዋላ ለማስወጣት መሞከር በጣም አደገኛ ስለሆነ ፈጽሞ እንዳትሞክሪ። አንድ ነገር ግን ቃልግቢልኝ። ገና ለገና አንዴ ሆኗል፣ በግድ አንቆ ቢደፍረኝም የልጁ አባት ነው ብለሽ ገብረብሩክ በተባለ አረመኔ ሰው ስም ልጅሽ እንዳይጠራ። እንደኔ እንደኔ ከሆነ፣ ከሁላችንም በተሻለ ሁኔታ በችግርሽ ያልተለየው መክብብ ስለሆነ በሱ ስም ቢጠራ እስማማለሁ። ካልሆነ ደግሞ ባባታችን ስም ይጠራ ወይም ትጠራ።

ስወ/ሮ አረጋሽ ግን በጣም አስጠንቅቀሽ ስለ አረመኔው ባሏ አስረጃት። እንደነገራችሁኝ ከሆነ በጣም ጥሩ ሰው ነች። ትምህርትም ስላላት ብልሃት አታጣም። ጉዱ እንዳይታወቅበት በተቻለው አቅም ከመጉዳት ስለማይመለስ ዘውትር ጥንቃቄ አይጉደልሽ። በጣም የሚያስደስተው ነገር ይህንን ደብዳቤ በወ/ሮ አረጋሽ በኩል እንዲደርስሽ ይዞልሽ የመጣው ልጅ ብዙ ጊዜ ጀርመን አገር እንደሚመላለስ ጓደኞቼ ነግረውኝ እንዲያስተዋውቁኝ ጓደኞቼን ጠይቄያቸው ነው ያስተዋወቁኝ። ባይገርምሽ ስለደረሰብሽ ሁኔታ አልፎ አልፎ ነግሬው እንባ ነው የተናነቀው። ብታይው እንዴት አዛኝ መሰለሽ። የራሱንዘዴ ተጠቅሞ አንቺን ለማግኘት እንደሚጥርም ነግሮኛል። ባገኘሽው ጊዜ ሁሉንም እጫውትሻል። ስሙ 'ነቢዩ' ይባላል። መልኩ ብቻ ሳይሆን ጸባዩም ደስ ይላል። ገበዝ ነጋዴም ነው ብለውኛል። ነጋዴነቱ ከብዙ ሰው ጋር ስለሚያገናኘው ብዙ

ሰው ያውቃል ይባላል። ለማንኛውም እግዚአብሄር ፈቅዶ ካገኘሽው በሚገባ አስረጂው። ስልኬ ያው ነው።

በተረፈ፣ ጀርመን ያው እንደለማነው ጀርመን ነው። ብዙም ሰውጥ የለ፣ ጉልበታችንን ይፈልጋሉ፣ እኛ በሄድንበት ባይሄዱ፣ እኛ በምንመገብበት ባይመገቡ ግን ደስታቸው ነው። እኛም ይህን ሁሉ ችለን አለነው እልሻለሁ።
አገራችን ሰላም እንደሆነች ዘውትር እሰማለሁ። ኢትዮጵያችን ግን ትናፍቀኛለች።

ምንጊዜም ያንቺው፣
እህትሽ

# ምዕራፍ ዐራት

ስልኩ ሲያቃጭል "ይቅርታ አረጋሽ" ብሎ "ሃሎ ተፈ!" አለ። ተፈሪ የባልቻው የምርመራ ቁጭ በሉ መሆኑ ነው። ንግግራቸው አጠቃላዩን ሌላ ቋንቋ ሆኗል። "አዎ! አይ፣ እሺ" ነው የሚለው፣ "ባብዛኛው ማንበቡን ቻለ፣ እኔ እንዲያውም ጥቁሩን ቀይ፣ ቀጭኑን ወፍራም፣ ነጩን መኪና ቢጫ ብሎ ቅንጣት ታክል እንዳላወቀ ተረድተናል።"
ገብረብሩክ "ዋው!" ብሎ እየተፍለቀለቀ ከመታጠቢያ ቤት ሲወጣ "እንዴ አሁን ባሁን ምን ተገኘ" ስትለው፣ በአመልካች ጣቱ "ቆይ እንዴ" አላትና "በይ እንግዲህ የዚህ ሁኔታ በአስተማማኝ ተጠናቋል፣ የቀረውን እንደምንም አፈላልጎ ጥሩ ሥራ ማስቀጠር ነው። ተግባባን!" ስልክ ተዘጋ። ወ/ሮ አረጋሽ ተስፋ ሳትቆርጥ "እኮ ምን ተገኘ??" ስትል አጥብቃ ጠየቀች።
"አይ አንድ ሰው አንድ ሥራ ለማስቀጠር በጣም እየሞከርን ነበርና በምንፈልግበት መ/ቤት መቀጠሩን ስለነገረኝ ነው።"
"አ!" ብላ "እራት ከበላህ ላቅርብ? እኔስ እህሉም መሮኛል።"
"አይ .. እኔም እንዳንቺው ነኝ።"

ገብረ·ይ ትኩር ብሎ ላየው ዐይኖቹ ውሸት ትጥፈት የማይወዱ፣ ክንዱ አጭበርባሪዎችን የሚደቁስ መሆኑ ያስታውቃል። ረዘም ብሎ ቀጠን ያለው ተክለ ሰውነቱ ዘወትር ከሚሰብሳቸው ሱፎች ጋር እግዜር ተጨንቆ ተጠቦ የሠራው ነው የሚመስለው።

ገብረብሩክ ትርሲትን ካጣሩ በሁዋላ የአባቷን የእቶ አምባዬን ሹራብ ቤት በስሙ ለማዛወር የሚያደርገውን ውጣ ውረድ እንነብራይ መከቸውም ግዜ በላይ በተጠናከረ ሁኔታ በበይን ቁራኛ እየተከታተለት ነው።

ጊዜው ይመሻል ይነጋል። ቀኖች ወደ ሳምንት፣ ሳምንቶች ወደ ወራት ዝም ብለው ይንጉዳሉ። መክብብም ከሆስፒታል ከወጣ በሁዋላ አንዲት ቀን ብቻ ሰወ/ሮ አረጋሽ በመደወል ደግሜ እስከምደውልልሽ ምንም እንዳታስቢ፣ ሌላ ጊዜ እደውላለሁ ካላት በሁዋላ የገባበት፣ የወጣበት ጠፍቷታል። ቢቸግራት ይማርበት ከነበረው ት/ቤት ሂዳ ብትጠይቅ "ውጤቱ እጅግ በጣም ጥሩ ስለሆነ ወደ ቀን ተዛውሮ የ12ኛ መልቀቂያ ፈተናን ለመፈተን ሲል ከዚህ መልቀቂያ ወስዷል" ብለዋት በየቀኑ የመክብብን ስልክ ትጠባበቃለች።

ከጥቂት ጊዜያት በሁዋላ፡ግን በህልሟም በእውኗም አስባው የማታውቀው ሰው ደወለ። "እትዬ አንዳትደንግጭ ትላለች" እየደጋገመች። ወ/ሮ አረጋሽ የምታውቀው ድምጽ ይመስላትና፡ ወዲያውኑ ይጠፋታል። ሴቶች እርግዝና ሲጫጫናቸው፡ ጉዳት ሲኖርባቸው ሰውነታቸው ብቻ ይሆን ድምጻቸውም ይቀየራል። ከተወሰኑ ቃለ ምልልሶች በሁዋላ ነበር "እትዬ ትርሲት ነኝ" ስትላት ቢሮው ያለው ሰው ሁሉ እስከሚሰበሰብ "ዋይ!" ብላ የጮኸች ው።

"የት ነው ያለሽው?!"

"ሩቅ ቦታ ነው፡ ብዙ ማውራት አልችልም፤ ለማንኛውም በእግዚአብሄር እርዳታ ይሄው ነፍሴ አለች እነሱማ ከእንግዲህ ተስፋ የላትም ብለው እንደ እባብ ቀጥቅጠው አመንገድ ላይ ከጣሉኝ በኂላ ለነፍሳቸው ደደሩ አለመሞቴን ካወቁ በኃላ ከመንገድ ላይ አንስተውኝ ይሄው እዚህ እድርሰውኛል፤ የቀረውን ስንገናኝ እናወራዋለን

እትዬ ለመሆኑ መክብብን እንዴት ነው የማገኘው?"

"እኛ ጋ አይኖርም፡ እደውላለሁ ብሎኝ ይኸው በየቀኑ እየጠበኩት ነው። አሁን ጊዜ ሳናጠፋ ያለሽበትን አድራሻና ስልክሽን ንገሪኝ፡"

"እትዬ በሌላ አትውሰጂውና መክብብን ካገኘሁት በሁዋላ አብረን እንድናገኝሽ ነው የፈለኩት፡ ለማንኛውም መደውሌን ካንችና ከመክብብ በስተቀር ማንም እንዳያውቅ፡ ሰሁላችንም ጥሩ አይመጣም።"



ወ/ሮ አረጋሽ እየተበሳጨችም እየተገረመችም ትርሲት ሚስጥር፡ መክብብ ሚስጥር እቤቴ ውስጥ አንድ ጉድ ተፈጥሮ እንደነበር አየከነከነኝ መጥቷል፤ በተለይ የገብረብሩክ ከቀን ወደ ቀን መለወጥ ራሱ አንድ አንቆቅልሽ ነው" ብላ አስበችና "ይሁን ደህና፡ ሁልጊዜ በዚህ ሰዓት ደውይልኝ፡ ሥራ ፋታ የማገኝበት ሰዓት ነው" ብላ እንባዋን እየረጨች ስልኩ ተዘጋ።

ገብረብሩክ ከሥራ ከታገደ ዋል አደር ብሏል። በቤታቸው ከባንክ ብር ተበድሮ አለበለዚያም ሽጦ ነጋዴ ለመሆን ፈልጎ ወ/ሮ አረጋሽ "አይሞከርም አይደረግም" ብላው ነጋ ጠባ ንዝንዝ ሆኗል። ወ/ሮ አረጋሽ ሰሞኑን በጣም የገረማት ደግሞ እንደ ህጻን ልጅ እየተሽቀዳደመ የቤቱን ስልክ ያነሳና የሚለው ነገር ሳይታወቅ ይዘጋዋል።

ከምሳ መልስ ከፊት ለፊት ያሉትን ወረቀቶች አስተካክላ ወደ ኮምፒተሯ ተሽከርካሪ ወንበሯን ስታዞር፡ በር ሲንኳኳ ዞር ስትል በህልሟም፡ በውኗም ያላሰበችው መልከ መልካም ወጣት ከቢሮዋ ልግባ ወይስ ልመለስ ብሎ ቆሞ ስታየው በሚገርም ፍጥነት ከወንበሯ በመነሳት "ጤና ይስጥልኝ የኔ ወንድም፡ ግባ" ብላ ወደ ወንበሩ እያሳየቺው፡ እየጨበጠችው "አረጋሽ" ስትለው፡ "ነብዩ" ብሎ ተጨባበጡ። "አረፍ በል፡ ሻይ፡ ቡና ወይስ ለስላሳ?" ብላም ጋበዘችው። "እኔ የምፈልገው ቢክስ፡ ከሌለም ሄንከን" ብሎ ፈገግ ሲል ወ/ሮ አረጋሽ ጊዜም አልፈጀባት፡ "እሽ ቢክስ ከጀርመን ነው፡ ሄኒከን ከሆላንድ፡ እዚያ ነው የምትኖረው፡ ነው ወይስ?" ብላ በጥያቄ ሀይትን ስታየው፤

"ግሩም ግምት" ብሎ ፈገግ ሲል፤

"እሺ ባሬ ምን እግር ጣለህ፡ ምን ልታገኘ አቶ ነቢዩ" ስትለው ነቢዩ ስለ ቢከስና ሄንከን ለጨዋታ መከፈቻ የተጠቀመው ዘዴ እያስገረመው ከሃሳቡ እየባነነ፤

" መልእክት ተልኬ ነው" ሲል፤

"ዉ.ዉ. ከምትደክም ብትደውልልኝ ይሆን ነበር"

"በመደወል የሚሆን አይደለም" እያለ ከኪሱ ደብዳቤውን አውጥቶ ሲሰጣት አይኗ ገና 'በወ/ሮ አረጋሽ በኩል ለትርሲት አምባዬ' የሚለውን ስታይ እጇ፡ ከንፈሯ፡ ሁለመናዋ ሲንቀጠቀጥ ነቢዩ ነገሩ ገባውና "ዐይኑን ዐይኗ ላይ በማሳረፍ፤

"አይዞሽ የማያልፍ ነገር የለም፡ ሁሉም ያልፋል ማድረግ ያለብሽን ነገር ጠንክር ብለሽ ማድረግ ነው" አላት።

"ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ እኮ የኔ ወንድም!" ብላ ከየት መጣ ከየት ሳይባል እንባዋ እንደ ደራሽ ውሃ ፊቷን አለበሰው። ነቢዩም ደነገጠ።

"በይ ወ/ሮ አረጋሽ እንዳልኩሽ ነው። ስትረጋጊ ደውይልኝ። ይህቺን ልጅ ለመርዳት መወያየት አለብኝ" ብሎ ጨብጧት ወጣ።

ደብዳቤውን አንዴ ወደላይ አንዴ ወደታች ብታደርገው እንደታሸገ ነው። እንዳትከፍተው ግብረ ገብ ማጣት ሆነባት። ትርሲትን እግኝታ ብትሰጣት እህቷ የትርሲትን ሁኔታ ሳታውቅ እንዲህ ሁኚ እንዲህ አድርጊ ብላ የባሰ ጭንቀት የሚፈጥርባት ከሆነስ" ብላ በሃሳብ ተውጣለች።

ሌሊቱንም ቀኑንም አሰላስላ አውጥታ አውርዳ በተለይ ነቢዩን ከማግኘቷ በፊት ደብዳቤውን ለማንበብ ወሰነች።



ገብሬይ ለስለላ ተግባር ከተሰማሩት ላቅ ያለ ስፍራና ክብር የሚሰጠው አገራችን ካፈራቻቸው ጠንካራ ባለሙያዎች ጎን ቢሰለፍ ስልፍ አያበላሽም። በተስፋይቱ ምድር አሜሪካም በሲ.አይ. ኤ ለታዳጊ አገር የሚሰጠውን አጠር አጠር ያሉ ኮርሶች ደጋግሞ ወስዷል። እስራኤል አገርማ ቅርበትም ስላለው ነው መሰል እንደ ውሃ መንገድ ተመላልሶበታል። ግሩም አዳኝ ወጥቶታል። የሚገርመው ገብረብሩክን እቆዳ ውስጥ የቀበረበት ችግስ ሳይኖር የሚቀር አይመስልም። ምክንያቱም በተለይ አሁን አሁን ገብረብሩክ የሚያደርገው ጥቃቅን ነገር በቀላሉ ትደርስዋለች።

ከወ/ሮ አረጋሽ ወይም ገብረብሩክ ለሌላ ሰው አውርቶ የሰማው ሳይሆን ገብረብሩክ መኖሪያ ቤታችን ካልተሸጠ ሞቼ እገኛለሁ እንደሚል ወ/ሮ አረጋሽም በፍጹም አልስማማም እንደምትል ጥርት ባለች ሁኔታ ለገብሬይ ይደርሰዋል። ገብረብሩክ ለጓደኞቹ "ሚስቴ ቤቴን ገዥ ሳገኝ አምርሬ እምቢ ካለች እተኛችበት እስከዘላለሙ እንድታሸልብ አደርጋለሁ" እያለ የሚፎልለውንማ ለራሱ ለገብሬይ እንደነገረው ያህል ነው እየቆጠረው ያለው።

"እግዚአብሄር አምላኬ ይቅር በለኝ የተቸገረን ሰው የምረዳበትን መፍትሄ ያገኘሁ መስሎኝ ነው እንጅ አደራ ላለማክበር ወይም የሰው ሚስጥር ለማወቅ ብዬ አይደለም" ብላ አማትባ ከፈተችው። ገና ማንበብ ስትጀምር ደብዳቤውን በእጇ ላይ አውሎ ነፋስ ካልነጠኩሽ የሚላት ነው የሚመስለው:::: በሚያስገርም ሁኔታ ተንቀጠቀጠች። እንደምንም እንባዋ ከጨረሰች በሁዋላ አንድ ጊዜ ብቻ "ዋይ ...! ባል ከጠረጴዛዋ

ሥር ድፍት አለች። በሃፊዋ ጩኸቷን ሰምታ "ውይ እህቴን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ወ/ሮ አረጋሽ፣ ወ/ ሮ አረጋሽ ምን ሆንሽ " ብትላት ብታቃናት ብታገላብጣት በድን ሆናለች። ፀሃፊዋ ጩኸቷን ለቀቀችው። ከየክፍሉ ሁሉም ተንጋግቶ ቢሮው ውስጥ ተሰገሰገ። የመሥሪያ ቤታቸው ነርስ "እስቲ እውጭ ውጡ አየር በደንብ ይግባ " ብላ ተገቢውን የህክምና እርዳታ ለማድረግ "አይዟችሁ" አለችና ሥራዋን ቀጠለች።

የገዛ እጇን በልቧ ላይ አድርጋ "ጫን ጫን" ስትላት በስፊው ተንፍሳ ዐይኗን ገለጥ አደረገችና ብዙም ሳትቆይ እንደተንጋለለች እንባዋ እየወረደ ጆሮቿን ሞልቶ ወለሉ እየረጠበ ነው። ሲስተሯም እንባዋ እያቀረረ "ምነው የኔ ሩሁሩሀ፣ ምነው የኔ እዛኝ፣ መካሪዬ ምን ሆንሽብኝ" ብላ ቀና ስታደርጋት፣ ደብዳቤው እንዳይቀደድ ልትቀበላት ብትሞክር "ተይው አይዘዋለሁ ሲስተርዬ" ስትል በስመመን ስሜት ተናገረች። "ግድ የለም ልቀበልሽ፣ አጣጥፌ ልሰጥሽ" ብትላት "ይሁን እኔው አጣጥፈዋለሁ" አለች መልሳ። ሠራተኛው ሁሉ መዳኗን ሲያይ ስታየን ትደነግጣለች ብለው ሁሉም ወደየቢሯቸው ተመልሰዋል።

ሲስተር ደብዳቤውን አለቅም ማለቷ አስገርሟት፣ "ለመሆኑ የምን ደብዳቤ ነው ልጄ፣ ከጤናሽ አይበልጥም እኮ? መጀመሪያ ራስሽን አስተካክለሽ ቀስ ብለሽ ታነቢዋለሽ" ..ገና ሳትጨርስ .."ሲስተርዬ እንብቤዋለሁ እኮ! ስንት ጉድ ይዟል መሰለሽ" ብላ ትክሻዋ ላይ ተለጥፋ እንባዋን ታዘራው ጀመር።



ብትላት፣ ብትሠራት ልትነግራት አልፈለገችም። "የቤቴ ጉድ ተዘርዝሯል፣ አያልቅም" ብቻ ነው እየደጋገመች የምትለው።

ትዝታ የወ/ሮ አረጋሽ የአለቃዋ ጸሃፊ ስትሆን፣ እንደ ወ/ሮ አረጋሽ የተዋጣላት ልቅም ያለች ቆንጆ ባትሆንም በቁንጅና ውድድር አሸናፊነቷ የተረጋገጠላት ይመስል ካለእኔ ቆንጆ የለም እንደምትል ሑኔታዋ ሁሉ ይናገራል። ስለትዝታ ግን በምትኖርበት ሰፈርም ሆን በምትሰራበት ቦታ ብዙ ሰው እንደምታውቅ ይነገርላታል። በተለይ አንዳንድ የሰፈሯን ሰዎች እንደየችሎታቸው የትም የትም እያለች ሥራ ማስገባቷ "ሕዝባዊ ኖሮ ዕድገት ትዝታ የዕርዳታ ድርጅት ...ብቻ ምኑ ቅጡ የማይጠሯት ስም የለም። እሷን የሚያስከፋት ከሷ ስለተሻለች ስለቁንጅና ሲወራ ብቻ ነው።

ወ/ሮ አረጋሽ ባለፈች ባገደመች ቁጥር አንዳንድ ወጣቶች በአድናቆት ሲያዩዋት ትዝታ ካየቻቸው "እነዚህ ደግሞ ከየት የመጡ ዐይን አውጣዎች ናቸው፣ ሰው አይተው አያውቁም እንዴ? እስቲ ቆይ አሁን ምኗ ነው እንዲህ ተፈጦ የሚታየው" ትላለች እየተልጎመጎመች።

ከመቼውም ጊዜ በማይመጣጠን በወ/ሮ አረጋሽ እርር ድብን ብላ የቀናችው፣ ልትግባባው ብዙ ጊዜ ሞክራ ያልተሳካላት ነቢዩ ከወ/ሮ አረጋሽ ቢሮ እንኳኩቶ ሲገባ ስላየችው ነው።

ዐይኗን ማመን አቅቷት እንደ ጨፈን፣ እንደ ገለጥ እያደረገች በእጇ ብትጠርገው ያው ነቢዩ ነው። ስለ ነቢዩ ሁኔታ እሷ እስከምታውቀው ዓለምን እየዞረ መነገዱ ሳይሆን የንጽህናው፣ የልብሱ፣ የሥነ ሥርዓቱ ብቻ ሴቶች የሚፈልጉት

አይነት ወንድ ተደርጎ የተፈጠረ ነው:: ብዙዎቹን ሴቶች የሚያስገርማቸው ደግሞ ዛሬ ተዋውቋቸው ነገ አብረን እንጻራ አይነት ይመስላቸዋል፣ ባህርይው ቸኮል ያለ ስለሚመስላቸው:: ነብዩ ግን የወንድ ጓደኛ እንዳለው ሁሉ ሴቶችም እንደወንድማቸው እንዲያዩት ስለሚፈልግ ብዙ ጓደኞቹ ሴቶች ከነባለቤታቸው ናቸው::

ትዝታ ግን ይህን ሁኔታውን ስላልተረዳችለት "ዋው ደግሞ ዛሬ ይች ነች ባለተራ፣ ምነው ልጁ ዛሬስ ቀለለ:: ደግሞ ዛሬስ ክዚች ከፉንጋ ጋር፣ ወይ ይችማ ስንጥር፣ ያቺማ ዝርዝኝ፣ ትንሽ ቆንጆት ካለችባት ደግሞ "እ..እ ! ይቺስ ሙጫ ነገ ነች የምትለቀው አይደለችም..."፣ ብቻ የማትለው የላትም:: "የዛሬውስ ጫን ያለቺው ሙጫ ነች፣ እቢሮዋ ድረስ አክለፍልፉ አመጣችው፣ በቃ አጁን ሰጥቷል ማለት ነው እሰው እቢሮዋ ኳትኖ ከመጣ፣ ውይ አሁንስ ናኩት፣" ትላለች እንደልማዷ ብቻዋን እያጉረመረመች::

ገብሬይ 6 ዓይን፣ 12 እግር አውጥቶ ገብረብሩክንና ወ/ሮ አረጋሽን እየተከታተለቸው ነው:: ወ/ሮ አረጋሽ እቤት ልትደርስ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ሲቀራት አንድ ሞተረኛ ትራፊክ ፖሊስ አስቆማትና "ይቅርታ እመቤት፣ ጥቆማ ደርሶን ነው፣ እንዴ ከመኪናዎ ወርደው ቢተባበሩን?

"ወይ ጣጣዬ አበዛዙ! ኧረ ምንም ችግር የለም፣ ምነው ምን ተፈጠረ" ብላ እንደወረደች "እይ፣ ያልተፈቀደ መሳሪያ ይዛለች ብለው ይሆናል፣ ይሁን" ብላ እራሷን እያረጋጋች ሌላው ሞተረኛው እሷን በጥያቄ ሲያዋክባት፣ በመኪና ተከትለዋት የመጡት የሷን መኪና ይበረብራሉ:: ብዙም



ሳይቆይ ለሞተረኛው ወ/ሮ አረጋሽ ሳታይ የሆነ ወረቀት ሰጡትና ከመቅጽበት የሆነ ቦታ ደርሶ ወረቀቱን ይዞ ተመለሰ:: ወዲያውኑ ወ/ሮ አረጋሽን በመጥራት "ይቅርታ የተሳሳተ ጥቆማ ነበር" ብለው በምስጋና ሸኟት::

እበሯጋ ገና ስትደርስ ቤቷ የአዕ አልመሰላት አላት::እውስጧ የታመቀውን ቃጠሎ ከፊቷ ላይ እንዳይነበብ፣ በተሰዶ ገብረብሩክን ስታየው እንዴት እንደምትሆን የተቻላትን ያህል እየተለማመደች ነው:: እንደፈራችው ብዙም ሳይቆይ ገብረብሩክ ገባ::ገና ሰላምታ ተለዋውጠው ሳይጨርሱ "ምነው ልጄ ለወደፊት ህይወታችን መሻሻል ቤት ተሽጦ አነስተኛ ቤት ይግዛ ወይም ከባንክ ብር እንበደርበት በማለቴ ባየሽኝ ቁጥር ፊትሽን ከሶ እንደጠጣ ሰው የምታኮሳትሪብኝ" እያለ ንዝንዝ ገና ሲጀምር ያወቀባት መስሏት ደንገጥ በማለት "ምነው ገብረብሩክ አሁንስ አበዛኸው፣ እሞኝ እኮ ነው የዋልኩት፣ አሁንም በደንብ አልተሻለኝም:: ተኝቸ ካገኘኸኝ ትደነግጣለህ ብዬ ነው ያልተኛሁት፣ በል ራትህን ሞቅ ሞቅ አድርገህ ብላ፣ ዛሬስ አልቻልኩም መተኛቴ ነው" ብላ ብድግ ስትል እንደገና በነገር ጠመዳት::

"እሱን እንኳን ተይው፣ ምንሽም የታመመ አይመስል:: አጉል መውረግረግ የት እንደሚያደርስሽ እናያለን " ብሎ ፀጥ አለ:: መተኛቷን ካረጋገጠ በኋላ ፍሪጁን ከፍቶ ወ/ሮ አረጋሽ የምታዘወትራቸውን ምግቦች ገለጥ ገለጥ ገልበጥ ግልብጥብጥ አድርጎ አያቸው:: ብዙዎች ምግቦች ሰሞኑን እንዳሉ ናቸው ከስራው ቢታገድም፣ ሰሞኑን መቸም በህይወት ዘመኑ እንደዚህ ትንፋሽ እስከሚያጣ እራሱን እንዲህ ታታሪ

አድርጎ አያውቅም። ስብሰባው ስልክ በየሱቁ መዞሩ ከየደላሎች ጋር መወዛገቡ ... ብቻ ስንቱ ታታሪ ሰራተኛ መሰሏል። ምጥጥ ያለው ፊቱ ግን የባሰ ግርጥት እንዳለ ነው። ግራና ቀኝ ያሉት ፀጉሮቹ አለልክ አድጎ ራስ በራነቱ ደን ተመንጥሮ በጫካ መሃል የተሰራ የአስፋልት መንገድ አስመስሎታል። በጣም የሚገርመው ያ ሲጠጣ አጠገቡ ጠረጴዛ ከሌለ ብርጭቆ የሚያስቀምጥ በርጩ እሱነቱን እስክከሚቀይረው ሙሽሽ ብሏል። ከሥራው ሲታገድ መኪናውም ስለተወሰደበት በየቦታው በእግሩ ስለሚንቀሳቀስ ለጤናው ጥሩ ሁኖለታል። ለካስ መኪናም የጤና ጠንቅ ነው።

ትርሲት ከወ/ሮ አረጋሽ ጋር በተነጋገሩት መሠረት አልፎ አልፎ እየደወለች ቢሆንም አሁን አሁን ግን መክብብም ሊያገኛት እንደሚፈልግ ስለነገራት እሷንም ሆነ መክብብን ለማግኘት ወስናለች። እነመክብብን ከማግኘቷ በፊት ከነቢዩ ጋር በህይወቷ ላይ ስለተፈጠረው ውጥንቅጥ ግልጽልጽ አድርጋ ስለነቢዩም ማንነት የተቻላትን ያህል አጣርታ ለመጠየቅ ወስናለች።ከነቢዩ በፊት ከነ ዶ/ር እስክስታና ዶ/ር ፋሲል ጋር ለመወያየት ሞክራለች። የሆነ ሆኖ እነሱ ስለ ወደፊት ህይወታቸው የተሻለ ገቢ የሚያስገኝላቸውን ለማግኘት ወደ ውጭ አገር ለመሄድ የሚያስችሏቸውን ሁኔታ ለማሳካት ከላይ ታች እየተሯሯጡ ነው። "ዘንጀሮም መጀመሪያ መቀመጫዬን ብላለች" እያሉ መተረት ጀምረዋል።

ከብዙ ውጣ ውረድ በሁዋላ ወ/ሮ አረጋሽ፣ መክብብ እና ትርሲት ከነቢዩ ቢሮ ውስጥ ተገናኝተው፤ እንደ በጋራ



የሚያውቁት እጅግ በጣም የሚቀርቡትና የሚወዱት ሰው ሞቶ መርዶ ተነግሯቸው ይመስላሉ አንባ በእንባ ሲራጩ፤ ለምን እንደሚያለቅሱ፣ ለምን እንደዚህ እንደሚሆኑ ነቢዩ እነሱ ከሚያውቁት በላይ ስለ ገብረብሩክም ሆነ ስለእነሱ አውቋል። ነብዩም በድንገት እንባው ዱብ ዱብ ብሎ ጠረጴዛውን የመስታወት መወልወያ የተረጨበት አስመሰለው፤ ስለላ የማያስፈልግው ምን አይነት ተቋም ይኖር ይሆን ኃይማኖት? ኸኸ የባሰ የስለላ መዋቅር ያለበትን እድር ዋው የባሰውን አታምጣ ሰው መርዶ እንኳን ተረድቶ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ከማግኘቱ በፊት የእውነቱን መሆኑን ሳያጣሩ መች ያቃምሱና እያለ ሲገረም ትርሲት ስቅ ስቅ ብሳ ስታለቅስ ነበር ከሀሳቡ የባነነ።

ነቢዩ በድንገት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በመክብብና በትርሲት መካከል ገብቶ ግራና ቀኝ እጁን በየትከሻቸው ላይ ጣል በማድረግ በቃችሁ፣ አይዟችሁ "ዩ አር ኢን ጉድ ሀንድ፣ ለሁላቹሁ የተቻለኝን ሁሉ ለማድረግ ቃል ገብቶላችኋለሁ። ምነው እየነገርኳችሁ፣ ተዉ በቃችሁ ብሎ ቆጣ ብሎ ቀና ሲል ወ/ሮ አረጋሽም እንባዋን ታዘራዋለች፣ እሷንም ጠጋ ብሎ በማቀፍ "ምነው የኔ እናት፣ ስንቱን ተነጋግረን፣ ጠንክር በይ እንጅ፣ ብሎ ልክ የታወቀ የኃይማኖት አስተማሪ እስከሚያስኘው ሰው "አያችሁ ሕይወት ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት ጠመዝማዛ መንገድ ነች፣ ከዚህ ከተወለጋገደ መንገድ ወጥቶ ቀጥተኛውን ጎዳና ሊያገኘው የሚችለው እዚያው እጠማማ መንገድ ገና ሳይጨርሰው እንጻይቀር ጤነኛ መሆን

ያስፈልጋል። ለመጨረስ ደግሞ ጤነኛ መሆን ብቻ ሳይሆን ትዕግስትም ያስፈልጋል፤ በተለይ በታዳጊ አገር የሚኖሩ ሰዎች እጅግ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው የህይወትን ቀጥተኛ መንገድ አግኝተው የሚጓዙት፤ ይህም እራሱን የቻለ ጉዳት አለው፤ አሳቸውና ፈጠን ብሎ ከወንበሩ ላይ ቆሞ አለ። አንድ ሁለት ጥያቄ ልጠይቃችሁ፤ ለምሳሌ በጦርነት አውድማ ላይ ከጠላት ጋር በሚደረገው ፍሊሚያ አጠገባችሁ ያለ ጓድ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ተመትቶ ቢሞት ወይኔ ወንድሜ ወይኔ ጓዴ እያላችሁ በመጮህ ከሬሳው ላይ መንከባለል ነው ወይስ እሱን የመታው ጥይት አናንተንም እንዳይመታችሁ ጠላትን ለማጥቃት ወይም ለመከላከል መሞከር? ሌላው ሁለት አገራቸውን ጥለው የተሻለ አገር ፍለጋ በበረሃ ሲጓዙ አንዱ በአውሬ ቢበላ ወይም በውሃ ጥም ህይወቱ ቢያልፍ፤ ጓዴን ወንድሜን በበረሃ ላይ ጥየ እንዴት እሄዳለሁ ማለት ነው ወይስ ሌላ የተሻለ መፍትሄ መፈለግ? ቡዙ ቡዙ ማለት ይቻላል።

ለማንኛውም ስለ እያንዳዳችሁ የደረሰባችሁን በደል የተቻለኝን ያህል አጣርቻለሁ። ከሶሥታችሁም በጣም እንገብጋቢው የትርሲት ጉዳይ ስለነበር" ብሎ ሳይጨርስ ወ/ሮ አረጋሽ በድንገት ብድግ ብላ "ትርሲት አንገት ላይ በመጠምጠም ልጄን ልጄን፤ እህቴን የኔ ቆንጆ ይህ ባለጌ ብላ ለቅሷዋን ለቀቀችው። ነብዩም ድምጽ አልባ እንባውን ያወርደው ጀምሮአል ለካስ ድምጽ ሳያወጡ የሚያፈሱት እንባ እራስ ይበጠብጣል፤ የደም ሥሮች በጣም ይወጣጠራሉ እንደሚባለው ነቢዩም በአንዴ እግዜር ተጨንቆ ተጠቦ የሠራው የሚመስለው መልክ መልካም ፊቱ ልውጥውጥ አለ። ፊቱን



በቀዝቃዛ ውሃ ታጥቦ ውሃ ጎንጨት ካለ በሁዋላ፤ "ያው እንግዲህ እንደነገርኳችሁ ባጭሩ የሁላችሁም ጉዳይ በአጭር ጊዜ ውስጥ መልክ መልክ እንደሚይዝ ከሚመለከተው የመንግሥት አካላት ጋር እየተነጋገርኩ ነው። ይህ ሁሉ ጥረቴ ሊስተካከል የሚችለው ግን እ የማዛችሁን ተፈጻሚ ካደረጋችሁ ብቻ ነው።

1ኛ) ወ/ሮ አረጋሽ በጸና እንደታመምሽ ሆኖ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ትተኛለሽ። ስለሁኔታው በደንብ የምታውቅ ዶ/ር ዘመዴ አለች። እሷ ማንም ሰው እንዳይጎበኛት ብላ መመሪያ እንድታስተላልፍ ተነጋግረናል። የ24 ሰዓት ልዩ ጥበቃም እንዲደረግ አድርገናል። በድንገት "ለምን ይኸ ሁሉ ጣጣ" አለች ወ/ሮ አረጋሽ።

"ታሪኩ ብዙ ነው" አላት ነቢዩ።

"ነገሩን ለማወቅ በቶሎ ንገረኝ" በሚል አኳሁዋን አንገቷን ሰበር፤ ግንባሯን ጠጋ አደረገችበት።

"ባለቤትሽ በቤታችሁ ይሸጥ አይሸጥ ስላልተግባባችሁና በትርሲት ላይ የፈጸመውን ወንጀል ነገ ዛሬ ታውቂብኛለች ብሎ በመፍራትና በመሳሰሉት በአንቺ ላይ ጉዳት ለማድረስ ብዙ ጥረት እያደረገ ስለሆነ መረጃዎች በደንብ ተሰባስበው በቁጥጥር ሥር እስከሚውል አንቺን ከአደጋ ለማዳን ስንል ነው" ሲላት፤ እሷ ያልነገረችውን በማወቁ አውነትም ከልቡ ሊረዳቸው እንደሆነ ግልጽ ሆነላት።

"2ኛ) ትርሲትና መክብብ እስከተወሰነ ጊዜ እኔና አናንተ ብቻ የምናውቀው መኖሪያ አዘጋጅላችሁዋለሁ" ሲል መክብብ በድንገት "እኔና ትርሲት እንኳ ሰሞኑን ወደ ሸንኮራ ለመሄድ

አስበናል ነቢዩ" ምን የተሰየ ሃሳብ ነቢዩ እንዳሰው ለማዳመጥ እየጓጓ::

"ምነው መሄዱ በጣም አስፈላጊ ነው፡ ትርሲት?"

"እይ እኔ ነኝ በጣም የገፋፋሁት:: መክብብ የማትሪክ ፈተናውን በጥሩ ውጤት ስላለፈ የደስ ደሱን ለአያቱ ለመንገርና እነም ልተዋወቃቸው ስለፈለግሁ ነው"

"ለመሆኑ ሸንኮራ የት አካባቢ ናቸው? ባልጢ እራ-ንቡት ዘመስቀል በካን ወ/ሮ አገር እራራቲ ማሪያም፡ ዮሃንስ ጠበል ያለበት አካባቢ" በማለት በሸንኮራ ውስጥ ያሉ ከተማዎችንና መንደሮችን ዘርዝሮ ሲጠቅስለት በመገረም "እንዴ! እኔ እዚያ ያደኩት እንኳን ይሆን ያህል ጠንቅቄ አላውቀውም፡ እንዴት ነው ነገሩ" ብሎ ፈገግ ሲል "አይዞህ ብዙም አታስብ፡ እኔም እዚያው አካባቢ ነኝ:: ለመሆኑ አያትህ ማን ናቸው?" ሲለው "አቶ ገብሩ ደስታ ይባላሉ" ሲለው "ዋው! አሳቸው ሰውዬ እስካሁን በህይወት አሉ እንዴ? አሳቸው እኮ አገራችን እንደ አገር ሆና እንድትቆይ ትልቅ አስተዋጽኦ ካደረጉት ጠንካራ አርበኞቻችን አንዱ ናቸው እኮ! ት/ቤት በነበርንበት ሰዓት ለምን ደጃዝማች፡ ፊታውራሪ፡ ቀኛዝማች፡ ቢያንስ ግራ አዝማች ያልተባሉት ሃይለ ሥላሴ በፋሽስቱ የጣሊያን ወረራ ጊዜ ከሸሹበት የእንግሊዝ አገር ከድል በሁዋላ ተመልሰው ንጉሥ ሲሆኑ የት እናውቅዎታለን ካሉት ጓደኞቻቸው ጋር በማበራቸው፡ ከዚያ በሁዋላም ክቡር ዘበኛ ከተቀጠሩ በሁዋላ ውስጥ ለውስጥ ወታደሩን በንጉሡ ላይ ቅስቀሳ እያደረጉ ነው ተብለው ክትትል ሲደረግባቸው ቀድመው በማወቃቸው



አመመኝ ብለው በዚያው ጠፍተው ቀሩ ይባልላቸው ነበር::

'ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝነሽ ተላላ፡

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ' የተባለው፡ እህ.. ብዙ ዓመት ወደሁዋላ አስሄድከኝ:: እርግጠኛ ነኝ ከአሳቸው አንደበት ብዙ እንደሰማህ:: ለመሆኑ ደህና ናቸው? እድሜያቸው ለመሆኑ ስንት ደረሰ? "ወደ 99 እየተጠጋ ነው" ሲለው "ውውይ! የኛ ትውልድ እኮ ውስታ የማያውቅ ሆኗል:: አያትህ እንዴት ግሩም ሰው መሰሉህ:: ባገኙን ቁጥር ስደብተር ስእስክርቢቶ መግዣ ብለው ወሸቅ የሚያደርጉብን እንዴት ያበረታታን ነበር መሰለህ:: እስከህይወቴ መጨረሻ ድረስ የማረሳው ምክራቸው የሁሉ ነገር ቁልፍ መክፈቻው ትምህርት ነው የሚሉት ነበር:: በዚህ ምክራቸውም "አያችሁ፡ ጣሊያን በዓለም ላይ በማንኛውም ጉዳይ ላይ መጠቀም እንዳይቻል የተከለከለን የመርዝ ጭስ በሕዝባችን ላይ ረጭቶ በተለያዩ በወቅቱ በነበሩት ዘመናዊ መሣሪያዎች እየታገዘ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሕዝባችንን የጨረሰው መሳሪያውም ሆነ መርዙ እንዴት እንደሚሠራ--- እንደሚቀመም በማወቁ ነው::

ለምታደርጉት ነገር ዓላማ ይኑራችሁ፡ ማለቴ ሃኪም፡ መሃንድስ፡ የመሳሰሉትን መሆን ነው የምፈልገው ካላችሁ ከጥረት ጋር መፈጸም ትችላላችሁ:: እንዳልኳችሁ ጣሊያን እንዲያ ሲፎጅን የገዛ ሽንታችንን እየጠጣን ታግለነው:: አዋርደን ከአገራችን ያባረርነው ለማይ ከፍ፡ ምድር ዝቅ ቢል የማንም ነጭ ጭባ ባሪያ አያደርገንም ብለን በመጽናታችን ነው:: ብዙ ጊዜ ለአላማ የተደረገ ነገር ይሳካል" ይሉን ነበር:: ከሁሉም በላይ በየቀኑ የማስታውሰው ምክራቸው "አያችሁ ልጆች፡

የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበረው ኬነዲ የተባለው እንዳለው «አገራችን ምን አደረገችልን ብቻ ሳይሆን እኛስ ምን አደረግንላት›› የሚለውን ዘወትር አትርሱ።

ለምሳሌ እናንተ በአረፍት ቀናችሁ ዛፍ መተክል ያለበት ቦታ ችግኝ አፈላልጋችሁ ብትተክሉ ውሃ የሚሸረሽረውን መሬት አፈሩ ተጠራርጎ እንዳይወሰደው ብትደፋፍኑ ለአገራችሁ አንድ ነገር አደረጋችሁ ማለት ነው። ወደፊት ተምራችሁ ሃላፊነት ቦታ ለትቀመጡ በምንም አይነት እንዳታደሉ። በተለይ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ ጉራጌ፣ ..በአጠቃላይ በአገራችን ውስጥ ያሉትን ጎሳዎች ሁሉንም በአንድ ሀይን ማየት አለባችሁ። ካላያችሁ ሰው ባይፈርድባችሁ እግዚአብሄር ይፋረዳችሁዋል። ትልቅ መቅሰፍት ነው የሚሆንባችሁ አድራችሁን ተጠንቀቁ።

እዚህ ጉዳይ ላይ በጣም እንድታተኩሩበት የምፈልገው ይህቺን ተራ ብልጠት እርስ በርሳችን እንዳንለማማ ለማድረግ ፋሽስቱ ጣሊያን የሚጠቀምበት ዘዴ ስለነበረ የዚያ ስለባ እንዳትሆኑ ፍርሃቴን ለመግለጽ ነው" እና የመሳሰሉትን ሁሌ አስታውሳቸዋለሁ። የሚገርም የሚደንቅ ነገር ነው። 'ለሞል ወርልድ!' "ሰው የማይገናኝበት ቦታ የለም" ይባል የለም! ይቅርታ ወ/ሮ አረጋሽ፣ ይከ ጎረምሳ ስመመን ውስጥ አስገባኝ እኮ!

ስለዚህ ጥሩ ነው በፈለግናችሁ ሰዓት ሰው መላክ ይቻላል። ከቻልክ ባል ስልክኞች መልእክት እንዲቀበሉልህ ተባበሩኝ በላቸው። ምናልባት እኔም ብቅ ብዬ አቶ ገብሩን



በዚያው አያቸው ይሆናል። ለመሆኑ መንገዱ ያው እንደበፊቱ ወጣ ገባ ነው?"

"አይ..ትንሽ ሻል ብሏል። ጤፍና ሰንዴ ለማጓጓዝ መኪና አነሰው ብለው ነው። እንጂ የሆነ ማአድን ወይም ነዳጅ ቢኖር ኖሮ ገና ድሮ አስፋልት ይገባ ነበር። ከሄድክ ግን ክረምቱ ሲወጣ ይሻልሃል፣ ጭቃው አያንቀሳቅስም።

"በጣም ይገርማል፣ የዚያ አካባቢ ልጆች በትምህርትም በንግድም ከፍ ያለ ደረጃ ላይ መድረሳቸው ይነገራል። ከራሴ ጀምሮ አንድም ነገር አለማድረጋችን እንዴት ያሳፍራል?"

"አይ ..አንዳንዶች እኮ አሰተባብረው የገርባዴን ድልድይ አሠርተዋል። አሁንም ቢሆን ለመርዳት ከታሰበ በተለይ በ/ት/ቤት ዙሪያ ብዙ መርዳት ይቻላል። ለምሳሌ ሸንኮራ ውስጥ ወደ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ እየኖረ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የለንም። በቅርብ ያለው የዑንጀሩ ብቻ ነው። ስንት ተማሪ በበሽታ ይጠቃል መሰለህ። የደረቀ ዳቦ፣ የሻገተ ጭብጦ እየበላ ረጅም ርቀት በመጓዝ እየደከመው የሚሰጠውን ትምህርት ነቅቶ ባለመከታተሉ እያንቀላፋ በትምህርቱ የሚሰንፈው .."

"በቃን በቃን፣ ሌላ ጊዜ እንመለስበታለን" ወደ ወ/ሮ አረጋሽ ፊቱን ዞር በማድረግ "እንግዲህ እቅዳችን ይህን ይመስላል። ባጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም መልክ መልክ ለማስያዝ እንሞክራለን" በማለት ወ/ሮ አረጋሽን አስናብቶ ትርሲትንና መክብብን ወደ ወንጀል ምርመራ ይዟቸው በረረ።

ነቢዩ የትርሲትንና የመክብብን በደል ለሚመለከተው ክፍል ጠቁሞ ጉዳዩ በሰፋትና በጥልቀት ክትትል እየተደረገበት

እንደሆነ ስለተነገረው ብዙ ሥራ ቀሎታል። ባሬ የግብረብሩክንና የግብረአበሮቹን አስነዋሪ ተግባር ከሚከታተለው የቡድን መሪ ጋር ሊገናኝ ስለሆነ ሰዓቱ እንዳያልፍበት እየበረረ ነው። መስቀል አደባባይ የመኪና ፍጥነት መለኪያ ቢኖር ኖሮ አላግባብ በመፍጠን በሚል የቅጣት ቲኬት ያገኝ ነበር። ትንሽ ከፍ ሲል ደግሞ ተቃራኒው ሆነበት። የአዲስ አበባ መንገዶች አብዛኞቹ ለፈረስና አህያ መጓጓዥ ተብለው የተሠሩት እንዳሉ ይመስላሉ። ብቻ በየትም ብሎ በየት መድረስ አይቀር ደረሰ።

ገና እቢሮው ሲገቡ ገብሬ ይ ከመቀመጫው በመነሳት "ማ፡ ማ እንደሆነ ምንም ሳይቸገር በየስማቸው እየጠራ ጨበጣቸውናአረፍ አረፍ አሉ። ወደ ነቢዩ ዞር አለና "ወደ ዋናው ጉዳያችን ከመግባታችን በፊት፡ አቶ ነቢዩ ስላንተ አጠር ያለ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። በእውነቱ ፖሊስ ሕዝብን ሳያቅፍ፡ ከሕዝብ ጋር ሳይተባበር፡ ለሕዝብ ፍቅርን ሰጥቶ ፍቅር ካልተቀበለ በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ ይቆጠራል። ይህንን ነው ካንተ ያገኘነው ትምህርት። እኛ ሌት ተቀን ብንለፋ፡ ብንደክም፡ እችላለሁ አሰራለሁ ብለን እየተከፈለን ነው። አንተ ግን ገንዘብህን፡ ጊዜህን ለእውነት፡ ለሃቅ ስትል ከእኛ የበለጠ አኩሪ ተግባር በመፈጸምህ፡ በህይወት ባለነውም፡ ለሃቅ በተሰዋው የሠራዊታችን፡ በአጠቃላይ ለእውነት በተሰለፉት ስም ከፍ ያለ ምስጋናዬን በሥራ ባልደረቦቸዋም ስም አቀርባለሁ" ብሎ ከመቀመጫው በመነሳት ተጨባብጠው ተቃቀፉ።



በውስጥ ከነበሩት አራት ሰዎች በተጨማሪ ሌላ ሁለት ሙሉ የፖሊስ ልብስ የለበሱ ቁመታቸው የረዘመሩ፡ ሰውነታቸው የጸነሰ ህይናቸውን ገልጠው ወዲያ ወዲህ ሲያደርጉት የሚያስፈራሩ ወንድማማቾች የሚመስሉ ገብሬይን እመሃከል አድርገው ከነትርሲት ፊት ለፊት ተቀመጡ። እንኳንስ ሴቷ ወንዶችም መደንገጣቸው አስታውቆባቸዋል። በተለይ የሁለቱ መርማሪዎች ድርቅ ያለ ፊገግታ አልባ ሰላምታ ደግሞ ምን ተፈጠረ፡ ምን ሊያመጡብን ነው ያሰኛል። ወጣም ወረደም ወደማይቀረው የጥያቄና መልስ ውጣ ውረድ እያመሩ ነው።

"አሁን ሰዓት ልክ ሰባት ሰዓት ከሰዓት በሁዋላ ነው። ካሁን ጀምሮ የምንነጋገረው በሙሉ ለመረጃ ስለሚቀዳ በተቻላችሁ አቅም ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለመናገር ሞክሩ። መቶ አለቃ ዘውድነህ ቀጥል" አለ ገብሬይ።

"አቶ መክብብ ታምራት የእንቁጣጣሽ ለት እንተ በምትሰሪበት ወይም በምትኖርበት በእቶ ገብረብሩክና ወ/ሮ አረጋሽ መኖሪያ ቤ ት ምን ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር?"

" ሦስት ሆነው ደበደቡኝ። ትርሲትንም እየገፈተሩ ይዘዋት ሄዱ።"

" እምንህ ላይ ነው የደበደቡህ?"

"ይኸው ጠባሳውም አለ። ሁለት ቦታ ፈንክተውኛል።"

"አዎ እኔም ይታየኛል። በግራ ሽኩል ግንባሩ ጠባሳ አለው። አሁንም ከግራ ጆሮው ከፍ ብሎ በጭንቅላቱ ላይ ሌላ ጠባሳ ይታየኛል።"

"የመቱህን ሰዎች ብታያቸው ታውቃቸዋለህ?"

" አዎ፣ በተለይ አንዱ እኮ የራሳቸው የጋሼ ጓደኛ ሁሌ እቤት የሚመጣ ነው።"

" ጋሼ ማናቸው?"

"ጋሼ የቤቱ ባለቤት ገብረብሩክ ናቸው"

"የአቶ ገብረብሩክ ጓደኛ ሆኖ እንዴት ይህንን ድርጊት በእናንተ ላይ ለመፈጸም ምን እንዳነሳሳው የምትገምተው ነገር አለ?"

"እኔማ ወዲያው ነው የተገለጸልኝ።"

"ለምን ወዲያው ለፖሊስ አላመለከትክም?"

"በእርግጥ አስቤ ነበር፤ ነገር ግን እሳቸውም ያው እንደፖሊስ አይነት ስለሆኑ ሂጄ የማመለክትበት ጣቢያ የሳቸው ወዳጆች ይሆናሉ ብዬ ፈርቼ ነው።"

" አቶ ገብረብሩክ እንደፖሊስ መሆኑን እንዴት አወቅህ?"

"መደንገጡ እስከሚያስታውቅበት ከው ብሎ፣ አይ እቤት ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲያወሩ ስምቼ ነው።"

"ምን እንዳወሩ ትዝ ይልሃል?"

"እ... የደህንነት ሥራ በጣም አስልችኝ፣ ሁሌ ራስን አለመሆን .. አስቀያሚ ..ሲባባሉ ስለሰማሁ ነው።"

"ሁሉም ፖሊሶች ለዘመድ፣ ለጓደኛ ያደላሉ ብለህ ታስባለህ?"

"አላስብም፤ ግን ማን ሃቀኛ ማን አምታች እንደሆነ ማወቅ ይቸግራል። የሚያምኑት ሰው ከጠቆመ ግን ለአእምሮም እርካታ ይሰጣል።"

"መጠቆም ስትል..?"



"እውነቱን ተናገር ካላችሁኝ እኔም ሆንኩ ትርሲት፣ አቶ ነቢዩ አይዟችሁ ስንት ለድሃ የቆሙ ፖሊሶች አሉ ብለው ባያግባቡን ኖሮ ሁሌ ፖሊስ እንደፈራን፣ እንደሸሸን እንደተደበቅን የምንኖር ይመስለኝ ነበር።"

"ለምን?"

"ሁሉም የአቶ ገብረብሩክ ጓደኛ ስለሚመስለን።"

" ባልቻ ሆስፒታል ተኝተህ ቃለ መጠይቅ ያደረጉልህ ፖሊሶች ነበሩ?"

"ሳቅ ብሎ፣ እንደማቀርቀር አለና፣ ወዲያው ቀና ብሎ .. አዎ ጠይቀውኛል። በጣም እንጂ! ፈገግታው ውደ መከሳተር እየተቀየረ"

"ፖሊሶችን ብታያቸው ታውቃቸዋለህ?"

"በሚገባ፣ አንዱማ ያው የመታኝና ትርሲትንም ያስቃየው ነውኮ።"

"አመሰግናለሁ፣ እቶ መከብብ! ሌላ የምትጨምረው ነገር ከሌለህ በኔ በኩል ጨርሻለሁ።

"በአእምሮዬ ውስጥ የታመቀውን እንድናገር እድል ስለሰጣችሁን እግዚአብሐር ይስጥልኝ።"

ገረመው ወደ ገብራይ ፊቱን በማዞር ይህቺ ልጅ ሁኔታዋ አላማረኝም። ላቧ በጣም ይወርዳል። ሀይን አገላለጧም ትክክል አይደለም" ሲለው ገብራይ "እኔም አይቻታለሁ። የክፍሉ ሙቀትና ድካሙም፣ ጠጋ ብሎ በጆሮው 'ነፍስ ጡር መሆኗንም አትዘንጋ' ብሎት ወዲያውኑ እስኪ አንድ 10 ደቂቃ ነፈስ ይበልብንና ስወ/ት ትርሲት አጠር ያለ ጥያቄ አቅርበን እንለያያለን።"

መክብብ ከመርማሪዎቹ ጋር ወጣ ሲል ትርሲት እዚሁ ይሻለኛል ብላ እዚያው እተቀመጠችበት ወንበር ላይ ተጣብቃ ቁጭ ብላለች:: አቶ ነቢዩማ የአደራ እህቱን ጥሎ ላለመውጣት አጠገቧ ቁጭ ብሎ በያዘው መጽሄት ፊቷን ያራግብላታል:: ነጭም ጥቁርም ያልሆነ ያ የቀይ ዳማ ስልክልክ ያለ ቆንጆዬ ፊቷ በላብ ተሸፍኗል:: ልስልስ ያሉ ውብ ከንፈሮቿ ደርቀው ኩበት እየሆኑ ነው:: በአጠቃላይ በመላእክቶች አማላጅነት የእግዚአብሄርን ታእምር በምድር ላይ እንዲህ አይነት ቆንጆ ሴት መሥራት ትችላለህ ለካ ሊያሰብል የተፈጠረችዋ ትርሲት፡ በዚች ባጭር ጊዜ ከደቂቃ ወደ ሰከንድ ትንፋሿ ሳይቀር እጥር እጥር እያለ፡ መልኳም ልውጥውጥ እያለ ነው::

ነቢዩ በድንገት ከአጠገቧ ብድግ ብሎ ወደ ገብራይ በመሄድ " ይህች ልጅ ሁኔታዋ አላማረኝም:: ቶሎ ቶሎ ብለን ብንሄድ አይሻልም? ሲለው "ልክ ነህ፣ በሉ እንግባ፣ ተባብለው ቦታ ቦታቸውን ያዙ:: ዘውድነህ ጥይቄውን በመቀጠል "ስምሽን ከነአባትሽ ብትነግሪኝ?"

"ትርሲት አምባዬ"

"ከአቶ ገብረብሩክና ከወ/ሮ አረጋሽ ጋር ዝምድና አለሽ?"

"የ..ያለኝም፣ የአባቴ ጓደኛ ነው"

ስቃይን በማየት እየደከመች መሄዷ ስለገባው እሚፈልገው ጉዳይ ላይ ለመግባት እየተቻኮለ፡ "ከእነ አቶ ገብረብሩክ ቤት ለምን ወጣሽ?"

"በግድ እየደበደቡ ነው የወሰዱኝ "



"እነማን ናቸው፡ እነ አቶ ገብረብሩክ ናቸው የደበደቡሽ?"

"ሌሎች ናቸው"

"የት ወሰዱሽ?"

"ደብድበው እመንገድ ላይ ጥለውኝ ሄዱ"

"ይህን አደጋ ያደረሱብሽን ታውቂያቸዋለሽ?"

"እንዱን ጣቱን የነከስኩትን አስታውሰዋለሁ"

"ጣቱን ስትነክሽው የደማ ይመስልሻል"

"አዎ"

"ነፍሰ ጡር ነሽ እንዴ?"

"የቻለችውን ያህል እየተቁነጠነጠች፡ እንባዋን ከላቧ ጋር እያፈሰሰች 'አዎን"

"ከማን እንዳረገሽ ልትነግሪን ትችያለሽ?"

"በግድ አንቆኝ ጭራቁ ነው" ብላ ከተቀመጠችበት ወንበር ወለሉ ላይ ዘፍ አለች:: ሁሉም ተደነጋግጠው ሊያነሷት ሊረባረቡ ዘውድነህ መቅጃውን ወደ ትርሲት አፍ ጋ ጠጋ በማድረግ "ማነው ጭራቁ ...አይዞሽ በርቺ.. ማነው ያስገደደሽ፡ ማነው ጭራቁ?"

" ገብረብሩክ" ብላ ጭንቅላቷን ወደ ነቢዩ እግሯን ወደ መክብብ አድርጋ ጸጥ ረጭ አለች::

ፖሊሶቹ ቅልጥፍ ቅልጥፍ ባለ ሁኔታ ማጓጓዥ አዘጋጅተው ወደ መኪና ውስጥ ሊያስገቧት መክብብና ነቢዩ ብቻ ሳይሆኑ ፖሊሶችም ጭምር ልብሳቸው በደም ተበክሏል:: የባሰ እነሱም ድንግጥግጣቸው ወጣ:: ትርሲትም "እ እ እ እ...እያለች ለመተንፈስ ትጣጣራለች::